# ምዕራፍ ስምንት

## ገዢውን ወደ ስፍራው መመለስ

*እንቆቅልሽ እስኪፈታ ድረስ እንቆቅልሽ ሆኖ ይቆያል።*

ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባታችን እውነታ "አዲስ ልደት" እየተባለም ይጠራል፤ ይህም በምድር ላይ እንደ ገዢዎች ያለንን ሕጋዊ ሥልጣን መልሶ የሚያስጨብጠን ነው። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችን ደግሞ ይህን ሥልጣናችንን ለመለማመድ የሚያስፈልገን ኃይል ወይም ችሎታችን ወደ እኛ መመለሱን የሚያሣይ ነው። እነኚህን ሁለት ጽንሰ ሀሣቦች በአግባቡ መረዳታችን በምድር ላይ በመንግሥቱ ባህል ውስጥ ሆነን ስንኖር ውጤታሞች እንድንሆን ያደርጉናል፤ ሁለቱም ገዢው ወደ ስፍራው እንዲመቀስና በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ስለ ሚጫወተው ሚና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

እስኪ አሁን ደግሞ እነኚህን ሁለት ጽንስ ሀሳቦች ጠለቅ አድርገን በመመልከት፤ አዲስ ልደትን ከውሃ ምንጭ ጉድጓድ፤ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ደግሞ ከሚፈስ ወንዝ ኃይል ጋር እያወዳደርን እንቃኝ።

### አዲስ ልደት፦
### የመንግስቱን ሥልጣን ወደ ስፍራው መመለስ

ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ የገዢውን ወደ ሰው ዘር መመለስ አስመልክቶ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል እንዲህ ሲል ዘግቦታል፤ "እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት *የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ* ይሆናል እንጂ።" ውሃ በዚህ እውድ የመንፈስ ቅዱስ ምሣሌ ነው። የአዲስ ልደት እውነታ፤ አሁን በእኛ ውስጥ የማያቋርጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት መኖሩን የሚያሳይ ነው። ለዘላለም የሚፈልቅና እንደ አዲስ የሚፈለቀለቅ፤ ንጹህና ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው። ከዚህ በውስጣችን ካለ የመንፈስ ውሃ ደህና አድርገን ያለማቋረጥ ስንጠጣ፤ ከመንግሥቱ ሕይወት ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነትን እናደርጋለን።

እስቲ ገዢው፤ በአዲስ ልደት በኩል የመንግሥቱን ሕይወት ወደ እኛ እንዴት እንደሚመልሰው በጣም በጥልቀት እንመልከት።



### የሰውን ልጆች ከአስተዳደሩ ጋር እንደገና ያገናኛል

የመንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ በመጀመሪያ በተቀበልን ጊዜ - የገዢውን ወደ እኛ መመለስ ያመለክታል - የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂ የሆነው የተርሴሱ ጳውሎስ በጽሁፎቹ ሁሉ ውስጥ በተደጋጋሚ የመንፈሱ "መያዣ" ሲል እንደገለጸው፤ እኛ አሁን የንጉሡ መሆናችንንና በሰማያዊው መንግሥቱም ወራሾች እንሆን ዘንድ እርስት እንደተሰጠን የሚያሣይ ነው።

> "በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው።"

> "አሁን፤ ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም ሊመጣ ያለውን ነገር ያረጋግጥልን ዘንድ የመንፈሱን መያዣ ሰጠን።"

> "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይሄውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፤ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።"

### የሰው ልጆችን ዜግነት በሰማይ እንደገና ያፀናል

ይሁን እንጂ፤ አስቀድመን እንደማንም በምድር ላይ ነዋሪዎች ነበርን፤ የንጉሡ ልጆችና የመንግሥቱም ሙሉ ዜጎች ለመሆን በቃን። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም"። ሰማያዊው ዜግነታችን የተሰጠን በራሱ በንጉሡ ነው፤ ይህም ዜግነት የሚያስገኘው ሙሉ መብትና ጥቅም ሁሉ አብሮ ተሰጠን።

### በሰው ልጆች በኩል መንግሥቱን ወደ ምድር እንደገና ይመልሳል

ገዢው በምድር በሚኖሩ የመንግሥቱ ዜጎች ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ምክንያት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ራሱ በምድር ላይ ነው። ይህ እንደገና ወደ ስፍራ የመመለስ ሂደት በመጀመሪያ የተከሰተው ንጉሡ - ልጅ በምድር ላይ እንደ ሰው ለመኖር በመጣበት ጊዜና ኢየሱስ በመጀመሪያ በደቀመዛሙርቱ ላይ መንፈስ ቅዱስን እፍ በማለት ለወደቀው የሰው ዘር በመለሰበት ጊዜ ነው። ሰማያዊው አስተዳደር በአዲስ ልደት በኩል በምድር ላይ ወኪሎች አሉት። ወደ ሰማያዊው መንግሥት የሚገቡ የምድር ነዋሪዎች ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን፤ በዓለም ላይ የመንግሥቱ አገዛዝ መስፋን ይበልጥ እየታወቀ ሊሄድ ግድ ነው።

## ከሁለቱ ዓለማት ጋር ግንኙነትን የመፍጠርና ወደማይታየው ዓለም መግባትን እንደገና ያድሳል

አዲስ ልደት፤ ከሰማይ ወደ ምድር እንዲሁም ከምድር ወደ ሰማይ የሚደረገውን የሁለትዮሽ ግንኙነትን እንደገና የሚያድስ ነው። ቀደም ሲል ከሁለቱ ዓለማት ጋር ግንኙነት መፍጠር ያልኩት ይህንን ነው። በመጀመሪያ የሰው ልጆች ከንጉሥ - አባት ጋር ፍፁም የሆነ ግንኙነት ነበራቸው፤ ይሁን እንጂ ለግንኙነቱ መንገድ የነበረውን ገዢውን ባጣን ጊዜ ይህን ግንኙነት አጥተናል። ከንጉሥ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደገና በመሠረትን ጊዜ፤ ያኔ እርሱ ወደ እኛ በቀጥታ ሲመጣና ሲገናኝ፤ እኛም ወደ እርሱ በቀጥታ ልንገባና ልንገናኝ እንችላለን። አዲስ ልደት ማለት፤ ንጉሡ በሚኖርበት በማይታየው ዓለም ውስጥ ተቀባይነትን ማግኘት ብቻ ላይሆን፤ የመንግሥቱን ዓላማ በምናገለግልበት በዚያ ገዢነትን መለማመድ ጭምር ማለት ነው። ቀደም ሲል በጠቀስነው፣ በሚከተለው ዘገባ ውስጥ ኢየሱስ ይህንኑ ማለቱ ነበር፤

> "እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል። በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ደግሞ እላችኋለሁ፤ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ፤ ከሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና"

## በሰው ዘር ውስጥ የንጉሡን ባህርይ እንደገና ይመልሳል

ይህ ጽንሰ ሀሳብ ኢየሱስ፤ ለፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ ያስተማረው ነው፣ ኒቆዲሞስ የአዲስ ልደትን ትርጉም ለመረዳት ሞክሮ የነበረ ነበር። "እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልኩ አታድንቅ።"

ይህ መግለጫ "አዲስ ልደት" ለሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቸኛው ዋቤ ቢሆንም፤ ዛሬ ዛሬ በግርድፉ ብቻ አዘውትረን የምንጠቀምበት፤ ነገር ግን ትክክለኛ ትርጉሙን የሳትንበት ክፍል ነው። ዳግም ልደት ማለት ገዢውን መቀበላችንንና በዚህም ሳቢያ፤ በመንግሥቱ ግዛት ውስጥ ዜጎች እንሆን ዘንድ ብቁ የሚያደርገን አዲስ ባህርይ እንደተሰጠን የሚያሣይ ነው። እንደገና እግዚአብሔርን የምንመስል ሆነናል። ጳውሎስ እንዳለው፤ "እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፤ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባና መስዋዕትን አድርጎ ስለ



እናንተ ራሱን አሣልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።" የንጉሡ ልጆች ነንና በመንፈሳዊ ሰሪታችን "DNA" ውስጥ ይህ ባህርይ በመኖሩ አሁን በዓለም ውስጥ ሊንጸባረቅ ይችላል።

## በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፡ የመንግሥቱ ኃይል እንደገና መመለስ ነው

አዲስ ልደት ወይም መለወጥ ለመንግሥተ ሰማይ ያዘጋጀናል፤ ይህም ማለት ከሰማያዊው መንግሥት ጋር እንደገና መገናኘትና ከንጉሡ ጋር ያለን ህብረት እንደገና መታደስ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለምድርም ያዘጋጀናል፤ ይህም ምድር ሰማይን እንድትመስል የማድረግ ተግባራዊ ግዳጃችንን ለመወጣት የአገዛዝ ሥልጣናችን እንደገና መመለስ ማለት ነው። የተለያዩ ልምምዶች በመሆናቸው ምክንያት እነዚህን እርስ በእርስ የሚቃረኑ ህሳቦች ከመንፈስ ጋር ማነጻጸር እፈልጋለሁ።

> **አዲስ ልደት ለመንግሥተ ሰማይ ያዘጋጀናል።**
> **በመንፈስ መጠመቅ ለምድር ያዘጋጀናል።**

ንጉሡ ልጅ በሰማያዊው አስተዳደር ወዳለው ወደ አባቱ ከመመለሱ ከጥቂት ጊዜ በፊት፤ ለደቀመዛሙርቱ ይህንን ነገራቸው፤ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ"። በዚህ ስፍራ ለተጠቀሰው "ኃይል" ለሚለው ቃል የግሪክ አቻ ትርጉም "ዱናሚስ" የሚል ሲሆን ይህም "ተአምራዊ ኃይል" ማለት ነው። "ተአምራት" ብለን ስለምንጠራቸው ነገሮች ቀደም ሲል ያደረግነውን ውይይት አስታውሱ። ተአምራት የሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ በምድር ላይ የመኖሩ መግለጫ ናቸው። በመሆኑም ይህ ኃይል የሚመጣው በቀጥታ ከሌላ ዓለም፣ ከሰማያዊ አስተዳደር ነው፤ ይህም ንጉሡን በመወከል በዓለም ላይ ሥልጣናችንን ለመለማመድ እንዲያስችለን ነው።

የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ይህንን የኢየሱስን ቃል ይዘግባል፤ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል" ብሎ ጮኸ። "ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ቅዱስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና።"

በተለወጥን ጊዜ መንፈስ በእኛ ውስጥ ያድራል። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ለንጉሡ መታዘዛችንና በእኛ ውስጥ አስቀድሞ የተቀመጠው በኃይል እንዲለቀቅ መፍቀዳችን ነው። አዲስ ልደት ሳያቋርጥ እንደሚፈስ ምንጭ ሲሆን፤ ጥምቀት ደግሞ ኃይል እንዳለው ወንዝ ነው፤ ይህም ልክ

ለሰው ልጆች መሻሻልና ለዕለታዊ ኑሯቸው የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ለማንቀሳቀስ፣ ለምሳሌ እንደወፍጮ ለመሳሰሉ፣ ኃይልን ከሚመግብ የውሃ ኃይል ጋር የሚመሳሰል ነው።

እስኪ አሁን ደግሞ በሰው ዘር ዐመጽ ያጣነውን ኃይል በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዴት እንደሚመልሰው እንመልከት።

## የመግዛትን ኃይል እንደገና ይመልሳል

አዲስ ልደት ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር የነበረንን ግንኙነት እንደገና የሚያድስ ሲሆን፤ ጥምቀት ደግሞ በአስተዳደሩ የተሰጠንን ሥልጣን መጠቀም የምንችልበትን ብቃት ያቀዳጀናል። ኃይል ሁኔታዎችን የመግዛትና የመቆጣጠር ብቃታችንን የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል። በፍጥረታዊው ምድርና በዓለም ላይ በሚያጋጥሙን የተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የበላይነትን ለማስፈን የግድ ሊኖረን የሚያስፈልግ ኃይል ይህ ነው።

## አስተዳደሩን ለመወከል የሚያስችለውን ብቃት ለሰው ዘር እንደገና ይመልሳል

የሰማያዊው አስተዳደር ወኪል ሆኖ እንደገና መሾም አንድ ነገር ሲሆን፤ በአስተዳደሩ መላክህን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማሳየትህ ግን ሌላ ነገር ነው። ጥምቀት ንጉሥህ ከአንተ የሚፈልገውን ማሟላትህን በተጨባጭ የምታረጋግጥበትን ኃይል ይሰጥሃል። የመንፈስ ስጦታዎች ጠቃሚ የሚሆኑት እዚህ ጋ ነው። በምዕራፍ ዐስራ ሰባት ላይ እንደምን መሰከተው፤ የስጦታዎቹ እውድ በምድር ላይ መንግሥታዊ የሆነ አስተዳደር ነው። ገዢው በሰማያዊው አስተዳደር የተሰጠንን ተግባራዊ ግዳጅ መወጣት እንችል ዘንድ ኃይልን ይሰጠናል። በመሆኑም ስጦታዎቹ እንግዳ የሆኑ ልዕለተፈጥሯዊ ክስተቶች ሣይሆኑ፤ ተግባራዊ የሆኑ አስፈላጊነት ያላቸው ስጦታዎች ናቸው።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "እኔስ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩኝ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደቀረበች እወቁ።" እየተናገረ የነበረው፤ አጋንንትን ማውጣት፣ ሰማያዊው መንግሥት ወደ ምድር መመለሱን የሚያሳይ የተጨበጠ ማስረጃ መሆኑን ነበር። ይህ ስለ እምነት ብንል፣ ስለ ፈውስ ወይም ስለ ተአምራት ብንል ለሁሉም የመንፈስ ስጦታዎች በተመሳሳይ የሚሠራ እውነት ነው። ስጦታዎቹ የእግዚአብሔር አስተዳደር ህልውና፣ ሥልጣንና ኃይል በምድር ላይ ለመስፈኑ ማረጋገጫዎች ናቸው። መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎቹን ወደ ኢየሱስ ልኮ፤ ገዢውን ለመመለስ ወደ ምድር የሚመጣው ንጉሡ - ልጅ እርሱ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ

> የመጠመቅ ኃይል
> የመንግሥቱን
> እውነታ ያረጋግጣል



እንዲነግረው ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ይህንን የሚመለከት ነበር። የማቴዎስ መጽሐፍ እንዲህ ይዘግበዋል።

> "ዮሐንስም በወህኒ ሣለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀመዛሙርቱ ሁለት ላከና የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ እውሮች ያያሉ፤ አንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምፃሞችም ይነፃሉ፣ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፣ ሙታንም ይነሳሉ፣ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል።"

ኢየሱስ ከሰማያዊው አስተዳደር እንደመጣና በምድርም ላይ የመንግሥቱን የበላይነት እያስፈነ መሆኑን ለዮሐንስ ማረጋገጫ እየሰጠው ነበር። ሁሉን ነገር ያብራራ የነበረው ከመንግሥቱ እንጻር ሲሆን፤ የዮሐንስም መልዕክት ይሄው በመሆኑ ኢየሱስ የሰጠውን መግለጫ እንደሚረዳው ያውቅ ነበር።

## የሰው ልጆች የንጉሡን ጥያቄዎች እንዲያረጋግጡና የመንግሥቱን መስፈን በተጨባጭ እንዲያሳዩ ያስችላቸዋል።

የማቴዎስ መጽሐፍ የኢየሱስን መግለጫ እንዲህ ሲል ይዘግባል፤ "ለአህዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል።" "ምስክር" የሚለው ቃል በጥቅሱ የሚያመለክተው ስለ አንድ ሁኔታ እውነት የሆነውን ነገር በመመስከር መናገርን ነው። ከላይ በተገለጸው ማብራሪያ ውስጥ የተጠቀሰው ይህ ቃል በጥንታዊው የግሪክ ቋንቋ "የተረጋገጠ ነገር" ማለት ነው። ለምሳሌም "የተሰጠ ማስረጃ" ሊሆን ይችላል። በጥምቀት አማካይነት ኃይልን ማስፈን፤ ስለ መንግሥቱ እውነታዊነትና የዓላማውን ሐቅነት ለዓለም የማሣያ አንድ መንገድ ነው።

## የሰው ልጆች የንጉሡንና የመንግሥቱንም ክብር ይገልጡ ዘንድ ብቃት ይሰጣቸዋል።

የጥምቀቱ ኃይል ሁሉን ቻይ የሆነውን የሰማይና የምድር ሁሉ ፈጣሪ ባህርይ ሥራዎች በሕይወታችን እንገልጥ ዘንድ ያስችለናል። መዝሙረኛው ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ጽፏል፤

> "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣
> የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል፣
> ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፣
> ሌሊትም የሌሊት እውቀትን ትናገራለች፣

ነገር የለም፤ መናገርም የለም

ድምፃቸውም አይሰማም።

ድምጻቸው ወደ ምድር ሁሉ፣

ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።

ከላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ክብር በባህርይ ቋንቋ ሊገልጸው ከሚችለው በላይ ነው። የሁሉም ዓይነት ዘሮች፣ ህዝቦችና ከየትኛውም ወገን የሆናችሁ ሰዎች ተመልከቱት፤ ይህ በማያቋርጥ ሁኔታ ለዓለም ሁሉ ፈጣሪ ጮኾ ምስክርነትን የሚሰጥ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም በገዢው በኩል የመንግሥቱ ዜጎች የሚያከናውኑት ተግባር ከሰው ልጆች ቋንቋና ባህል አልፎ የሚሄድ ነው። ቋንቋውን መናገር ወደማትችለው ወደ አንድ አገር ብትሄድና፤ ገዢውም ለዓመታት ያህል ሽባ ሆኖ ለኖረ ሰው አንተን ተጠቅሞ ፈውስን ሊያመጣ ቢፈልግ፤ እርሱ የአንተን ቃላት ከመረዳት ጋር ጉዳይ የለውም፤ ምክንያቱም ድርጊትህን ሊረዳው ይችላልና ነው። ክብር የሚለው ቃል የሚገልጸው የአንድን ነገር መሠረታዊ ባህርይ ነው። አንድ ሰው በግል የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት የንጉሡ ባህርይ መሆኑንና፤ እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ኃይል እንዳለው ወደ መረዳት ሊመጣ ይችላል። ስለዚህ ንጉሥና ስለመንግሥቱም ለመስማት ጆሮዎቹን ይከፍታል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ፤ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ" እንዳላቸው ማለት ነው።

## የሰው ልጆች የሰማይ ዜጎች መሆናቸውን ማሣየት የሚችሉበትን ብቃት ይሰጣቸዋል።

ይህንን አስመልክቶ፤ በጥምቀት በኩል የተገለጸው ኃይል የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች መሆናችንን የሚያረጋግጥ ነው። ልክ እንደ ፓስፖርት ነው፤ እኛ የንጉሡ መሆናችንንና የመንግሥቱንም ሥራ ልንሠራ እውቅና የተሰጠን መሆኑን ያረጋግጥልናል። የመንግሥቱን ሥራ ለመሥራት "መሞከር" ብቻውን በቂ አይደለም፤ ሥራህን ለመስራት የሚያስችልህ የሥልጣን ድጋፍ የግድ ያስፈልግሃል። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጸው የአስቄዋ ሰባት ልጆች የገጠማቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ይኼው ነበር። ጳውሎስ በኢየሱስ ስም አጋንንትን ማስወጣቱን ያውቁ ስለነበር፤ እነርሱም ደግሞ እንደዚያው ለማድረግ ሞከሩ። ነገር ግን በሰማያዊው መንግሥት እውቅና ያለው ሥልጣን ያላቸው አልነበሩም፤

"የካህናትም አለቃ ለሆነ አስቄዋ ለሚሉት አንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት። ክፉውም መንፈስ ግን መልሶ፤ ኢየሱስን አውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤



እናንተስ እነማን ናችሁ? አላቸው። ክፉውም መንፈስ ያለበት ሰው ዘለለባቸው፤ ቆስለውም ከዚያ ቤት ራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው፤ አሸነፋቸውም። ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፣ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፤ የጌታም ኢየሱስ ስም ተከበረ።"

ጳውሎስ የሰማያዊው መንግሥት ሥልጣን ያለው ዜጋ ነበር፤ በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ያለውን ሥልጣን የጨለማው መንግሥት ወኪሎች ያከብሩትና ይታዘዙትም ነበር። የሰማያዊውን መንግሥት ኃይል በቀላሉ ከቶ ልንጠቀምበት አንችልም፤ ነገር ግን በውስጣቸው በሚኖረው መንፈስ በኩል በንጉሡ ሥልጣን የተሰጣቸው ብቻ ኃይሉን ይጠቀማሉ።

## ገዢውን በሕይወትህ መቀበል

በሚቀጥሉት ምዕራፎች፤ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኩል ስለሚመጣው ኃይል ሰፋ አድርጌ አብራራለሁ። አሁን ግን፤ በግል ሕይወትህ ገዢውን እንዴት መቀበል እንደምትችል እንድታተኩር እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ይህ በመጀመሪያ ደረጃ ከንጉሡ - አባት ጋር ያስታርቅሃል፤ እንዲሁም የመንግሥቱን ሥልጣን መቀበል እንድትችል ብቁ ያደርግሃል።

በአዲስ ልደት በኩል እርቅን ስለማድረግ ልትሰማ ከምትችላቸው መልካም የምስራቾች ሁሉ የላቀው ነው! ይህም ማለት ንጉሡን ያለ ፍርሃት ልትቀርበው ትችላለህ ማለት ነው። ኢየሱስ ስለ ዐመጽህና ከመንግሥቱ ነፃ ስለመውጣት መንፈስህ ይገባህ ስለነበረው ቅጣትህ ዋጋ ከፍሏል። በበዓለ ሃምሣ ቀን ተሰብስበው ለነበሩ ህዝብ የኢየሱስ ደቀመዝሙር የነበረው ጴጥሮስ በተናገራቸውና እየሆነ ስለነበረው ነገር በገለጸላቸው ጊዜ፤ ህዝቡ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጠየቁ። እንዲህም ሲል ገለጸላቸው፤ "ንስሃ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ።" በመሆኑም አዲስ ልደትን ታገኙ ዘንድ እናንተ . . .
.

በመጀመሪያ፤ *ንስሃ ግቡ*። በሰማያዊው መንግሥት መለኪያና መስፈርት አኳያ እንዴት መኖር እንደሚገባችሁና እንዴትስ ልትኖሩ እንደምታቅዱ አመለካከታችሁን ለውጡ።

ሁለተኛ፣ *በኢየሱስ መስዋዕትነት የተገኘውን ምህረት ተቀበሉ*። ዛሬ ዛሬ በሰው ልጆች ዘንድ ካሉት ዋንኛ ችግሮች አንዱ፤ ከንጉሡና ከመንግሥቱም ባህርይ ተፃራሪ በሆነ መንገድ ለሠራናቸው ስህተቶች የሚሰማን ከባድ በደለኝነት ነው። ይቅርታ ማድረግ ማለት ከተጠያቂነትና ከወንጀለኝነት ነፃ ማድረግ ማለት ነው። በመሆኑም በመንግሥቱ ነፃነት ውስጥ ለመኖር በኢየሱስ በኩል የተሰጠህን ይቅርታ የግድ መቀበል

ይኖርብሃል፤ ከዚያም በኋላ ጳውሎስ እንደጻፈው፤ "በአዲስ ሕይወት" ተመላለስ።

አንድ ጊዜ ከላይ በጠቀስኳቸው ደረጃዎች ካለፋችሁ፤ በውስጣችሁ *የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ።* ይህ የርስት መያዣና ወደ *መንግሥቱ ለመግባት ማረጋገጫው ነው። ይህንን በዋጋ የማይተመን ስጦታ ስለሰጣችሁ ለንጉሥ - አባት ምስጋና አቅርቡ።*

ይህን ልብ እንበል፤ በተጨማሪም *በውሃ እንድንጠመቅ* ትእዛዝ ተሰጥቶናል። በኢየሱስ ስም *በውሃ መጠመቅህ፤ ለኢየሱስ መንግሥት* ትምህርት ቤት ራስህን አሳልፈህ መስጠትህን፣ ከዚህ በኋላ እርሱ ጌታ *መምህርህ ለመሆኑና ለእርሱም ታማኝ መሆንህን እንዲሁም ስለ ዐመጽህ* ሁሉ ሙሉ ምህረትን መቀበልህን የሚያሳይ ነው።

አዲስ ልደት ማለት ሕይወትን ከዚህ በኋላ በራስህ መንገድ ልትመለከት አለመሞከር ማለት ነው። ንጉሡ ያንን ሸክምና ጭንቀትህንም አስወግዶታል። ልክ አንድ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያለ አገር *መንገዶችን ለመሥራት፣ የውሃ አቅርቦትንና የመሣሰሉትን ለማግኘት* በገገርው መንግሥት ላይ እንደሚደገፍ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ የመንግሥቱ ዜጋ በሕይወቱ ለንጉሡ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጥ ከሆነ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ይቀርቡለታል። ለዚህም ነው ኢየሱስ እንዲህ ያለው፤

> "እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንን ሁሉ አህዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፤ ስለዚህም ስለ ነገ አትጨነቁ፤ ነገ ስለራሱ ያስባልና።"

*የመንግሥቱ* ሕይወት ይህ ነው፤ በቅድሚያ *የመንግሥቱን መልካምነት መፈለግ፤* ቀጥሎም በሰማያዊው ገዢ በኩል በሰጠህ *ሥልጣንና ኃይል እርሱን እያገለገልክ ሁሉንም ፍላጎቶችህን ያሟላልህ* ዘንድ መፍቀድ።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ግንኙነትን እንደገና የመመሥረት ውጤቶች

*የዓሣ ስኬታማነት በውሃ ውስጥ መቆየቱ ነው።*

ማንም ሰው ያለገዢው፤ የሰማያዊው መንግሥት ዜጋ ሊሆን አይችልም። ዮሐንስ በወንጌሉ የኢየሱስን ቃል እንዲህ ሲል ይዘግበዋል፤ "እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው።"

አንድ ሰው ብዙ ጥቅም ያላቸውን ነገሮች ሊያከናውን፣ መልካም በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ሊሣተፍ እንዲሁም ሃይማኖታዊ የሆነ መነሻም ሊኖረው ይችላል፤ ይሁን እንጂ የመንግሥቱ መንፈስ የሌለው ከሆነ በመንግስቱ ውስጥ ያለ ሰው አይደለም። የሰማዩ ንጉሥ ሃይማኖታዊ በሆኑ ልምምዶችና የመስዋእት ሥርዓቶች የሚደሰት አይደለም። ልክ ዲራይቦ ኒኩሊክ አሲድ (DNA) የተባለው ንጥረ ህዋስ የአንድን ሰው ማንነት እንደሚወስን ሁሉ፤ በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ የመንግሥቱ ዜጋ አድርጎ ይፈርጀዋል። እዚህ ጋ ስስህተት ዳርቻ የለም።

በገዢው በኩል ከንጉሡ ጋር ግንኙነትን በጀመርክበት ጊዜ ሙሉ ለሙሉ አዲስና አስደናቂ ሕይወት ይከፈትልሃል። በመንግሥቱ የሕይወት ሥርዓት ውስጥ እንዴት እንደምንኖር፤ በገዢው የምንሰጥንባቸውንና በምድር ላይ ከእርሱ ጋር የአገዛዝ አጋሮቹ የምንሆንባቸውን የተወሰኑ መንገዶች ከመመልከታችን በፊት፤ ገዢውን ወደ ሕይወታችን በምንቀበልበት ጊዜ የሚከሰቱትን የመነሻ ሽግግሮችና ጥቅሞች በከሰሣ መልክ እንመልከት።

### ከንጉሥ - አባት ጋር እንደገና የታደሰ ዝምድና

ግንኙነትን እንደገና የመፍጠር የመጀመሪያው ውጤት ከንጉሥ - አባት ጋር ዝምድናን ነው። የሰው ልጆች ከሰማያዊው አስተዳደር የመለየት ነጻነት ባወጁ ጊዜ፤ ከሕይወት ምንጭ ራሳችንን አገለልን፤ ጎስቋሎችና ግራ የተጋባን ሆንን፤ እናም ሕይወት ዛሬ በምድር ላይ እንዲህ ባለ ጥፋት፣ አመጽ፣ ሰቆቃና አቅም አልባነት ውስጥ የተዘፈቀችው ለዚህ ነው። ምድር አንድ ትልቅ እቅድ እንዳለው ነገር ግን ይህን እቅድ ለመተግበር ግን የገንዘብ አቅም የሌለውን ሰው ትመስላለች።

ገዢው ወደ አንድ ሰው ሕይወት በገባ ጊዜ፤ ያንን ሰው ከራሱ የሕይወት ምንጭ ጋር ያገናኘዋል፤ ከፈጣሪው ጋር ዝምድና ይሰጠዋል - ዝምድናው ፈጣሪውን እንደ ንጉሥ ብቻ ሳይሆን እንደ ሰማያዊ አባቱ ጭምር ያደርግለታል። አሁን የንጉሡ የቅርብ ቤተሰብ ሆኗል፤ ማንኛውም የሰማያዊው ንጉሣዊ ቤተሰብ አባል ያለው መብትና ጥቅም ተካፋይም ነው።

ከንጉሥ አባታችን ጋር በተስማማን ጊዜ፤ "የመጣሁት ከአንተ ዘንድ ነው፤ እናም በአንተ ልደገፍ የግድ ነው፤ በአንተ ላይ እታመናለሁ" ብለን ማረጋገጫ እየሰጠን ነው። በእግዚአብሔር የመደገፍ ግዴታ ውስጥ እንኖራለን። ነቢዩ ኢሣያስ እንደተናገረው፤ አለቅነት በንጉሡ ጫንቃ ላይ ነው። እርሱ ህዝቡን ሲመራ ሃላፊነት አለበት። እርሱ የተጠራባቸው ስሞች የሚያመለክቱት ሃላፊነቱን ብቻ ሳይሆን ችሎታውን ጭምር ነው፤ ለምሣሌም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ የሚሉት ስሞች ለእኛ ማድረግ የሚችለውን አቅሙን የሚያሳዩ ናቸው።

## ልዩነትና ክፍፍል ወደሌለበት መንግሥቱ መግባት

ግንኙነትን እንደገና የመመስረት ሁለተኛው ውጤት፤ ልዩነትና መከፋፈል ወደሌለበት መንግሥት መግባት ነው። ቀደም ሲል፤ የአብን የተስፋ ቃል መምጣት አስመልክቶ የነቢዩን ኢዮኤልን ቃል ተመልክተን ነበር፤

> "ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፣ መንፈሴን በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሣለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ህልምን ያልማሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈሣለሁ።"

ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሣ ቀን የጠቀሰው ይህንን ትንቢት ነው። ጴጥሮስ የሰጠውን መግለጫ ያደምጡ የነበሩ ሰዎች፤ ይህ እነርሱ ከሚያውቁት ሕይወት እጅግ ልዩነት ያለው ሆኖባቸው ነበር። የገዢው መመለስ በምድር ላይ ለሚኖሩ የማንኛውም መንግሥት ዜጎች ወንዶች ቢሆኑ ሴቶች፣ ወጣቶች ቢሆኑ አዛውንቶች ሕይወት ክብርንና ዋጋ ያለውን ያለልዩነት ያረጋገጠ ነበር። በቀደመው ጊዜ ግን፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ፊት መሆን የሚችለው ሊቀካህኑ ብቻ ነበር። እርሱም ቢሆን ይህን ማድረግ የሚችለው በመስዋዕቱ ደም ከተቀደሰ በኋላ ብቻ ነበር። በተጨማሪም ካህናት መሆን የሚችሉት ወንዶች ብቻ ነበሩ። ይሁን እንጂ ጴጥሮስ እዚህ የኢዮኤልን ትንቢት በመጥቀስ፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሱ ይፈሳል ሲል ተናገረ።

ከዚያ በኋላ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ይቀበሉ ዘንድ በካህኑ በኩል መሄድ አላስፈለጋቸውም። ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ዘንድ



የሚመጣላቸውን ቃል ይሰጧቸው ዘንድ በነቢያት ላይ መደገፍ አላስፈለጋቸውም። መንፈሱ በእነርሱ ላይ ይፈሣል፤ ከንጉሡ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ይኖራቸዋል።

ዛሬ፤ እጅግ ብዙ ሰዎች "ከጌታ በፊት የነበሩ ልምምዶች" ብዬ በምጠራቸው ልማዶች ተይዘዋል። የገዢው መምጣት ጊዜው ያለፈባቸው (ኋላቀር) ያደርጋቸው ልማዶች ናቸው። ለምሳሌ ያህል፤ አንዳንድ ሰዎች ኃጢአታቸው ሲሰረይ የሚችለው ለካህን የተናዘዙ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። ይህ በኢዮኤል ዘመን የነበረ መንገድ ነው። አንድ ሰው ብቻ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ወዳለው የእግዚአብሔር መገኘት ይቀርባል፤ ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖርህ ያስችልሃል - ያም ሰው ካህኑ ነበር። ኢዮኤል እንዲህ ነበር ያለው፤ ይሁን እንጂ ንጉሡ ልጅ ይህ ሥርዓት እንዲያከትም (ያበቃለት) የሚያደርግበት ቀን ይመጣል፤ ምክንያቱም እርሱ የሚያቀርበው መስዋእት የኃጢአታችንና የዓመጸኝነታችን ሙሉ ስርየት ይሆናል። በዚህ በምትክነት በተደረገ ሞቱ ምህረትን የተቀበለ ማንኛውም ሰው፤ ወደ ንጉሥ አባት መገኘት መቅረብ ይችላል። ማንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም በገዢው በነሱ መኖር ቅድስተ ቅዱሳን በውስጣቸው ይሆናል! ምናችንም ቢሆን - ንስሃችን ይሁን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማወቃችን ቢሆን፣ ዝማሬያችን ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ጉባኤዎች መሄዳችን፤ ከእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖረን አያደርገንም። የንጉሡ ልጅ መስዋእት ብቻ ከኃጢአት *ሁሉ* ያነጻናል፤ ገዢውም በእኛ ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል።

በተጨማሪም ደግሞ፤ በቀደመው ሥርዓት ውስጥ ማንኛይቱም ሴት ካህን ትሆን ዘንድ አትጠበቅም። ይሁን እንጂ ኢዮኤል፤ የጌታ ቀን በመጣ ጊዜ ንጉሡ ገዢውን ያለ ምንም ጾታዊ ልዩነት ለማንኛውም ሰው እንደሚሰጥ ይነግረናል። "ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ" ይለናል። ስምንድን ነበር "ሴቶች ልጆች" የሚለው ቃል የተጠቀሰው? ይህ የሆነው የመንግሥቱን ባህርይና መጠን ለማሳየት ነው። የኢዮኤል ትንቢት እንዲህ የሚል እንድምታ ያለው ነበር፤ ንጉሡ ወደ ምድር የሚመጣበትን ቀን አያለሁ፤ በጾታ ረገድ የተደረገውን የሰዎችን ክፍፍል ያጠፋዋል ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ትንቢትን ይናገራሉ፤ ይህም ማለት የአገር ቤቱን መንግሥት ህሣብና ልብ በቅኝ ግዛት ላሉት መናገር ይጀምራሉ" ማለት ነው። "ትንቢት" የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ ትርጉም፤ "ሊመጡ ያሉትን ሁኔታዎች አስቀድሞ መናገር"፣ "መጭውን ማሣወቅ" ወይም "በመነዳት ውስጥ ሆኖ መናገር" ማለት ነው። እግዚአብሔርን ወክሎ ሲመጡ ስላሉት ነገሮች መናገር ማለት ነው። ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ከሰማያዊው ህሣብ ጋር መገናኘት ይችላሉ። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም። ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፤ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

በኢዮኤል ውስጥ የሚቀጥለው ቃል፤ "ጎልማሶቻችሁ ራዕይን ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ህልምን ያልማሉ" የሚል ነው። "ወጣት ካህናቶቻችሁ ራዕይን ያያሉ" ወይም፤ ሽማግሌ ካህናቶቻችሁ ህልምን ያልማሉ" አልነበረም ያለው። ገዢው ያላቸው ሰዎች ሁሉ ይህን ለማድረግ ህጋዊ ናቸው። ህፃን ልጅ፤ ወጣት፣ ጎልማሣ መሆንህ ወይም የቆየ ዜግነት ያለህ መሆኑ የሚያመጣው ለውጥ የለም፤ ገዢውን ወደ ሕይወትህ ልትቀበለው ትችላለህ፤ እርሱም በመንግሥታዊ ዓላማዎች ተካፋይ እንድትሆን ያደርግሃል። በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ የእድሜ ልዩነት የለም።

> **በሰማያዊው መንግሥት የሰው ባህላዊ ልዮነቶች ይጠፋሉ።**

ከዚያም፤ ባጋጣሚ ሃሳቡን ብንዘነጋ፤ ኢዮኤል እንዲህ ይላል፤ "በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ።" ንጉሡ ያለውን ነገር ራሱ እንደገና እንዲህ ሲል እየደገመው ነበር፤ "ጾታን፣ ዕድሜንና ማህበራዊ ማበላለጫዎችን አስመልክቶ በሰው ባህል ውስጥ ያሉ እንቅፋቶች ጠፍተዋል፤ በምድር ግዛት ላይ መንፈሴን ባፈለስኩ ጊዜ፣ ማንኛውም ሰው መንፈሴን ሊሞላ ይችላል።"

እንደገናም፤ ንጉሡ *በሰጋ ለባሽ ሁሉ* ላይ መንፈሱን ለማፍሰስ ይፈልጋል። በምድር ላለ ለማንኛውም ሰው ገዢው ያስፈልገዋል። ያለ መንፈስ ቅዱስ የሆኑ፤ ይገንዘቡትም አይገንዘቡትም፣ እርሱን እንዳጡት ይሰማቸዋል፤ በሕይወታቸው የጎደለውን ነገር ለመሙላት ድንገት ሲፍጨረጨሩም ያገኙታል። ከሁሉም ይልቅ ደግሞ እምነት የሌላቸው በከፍተኛ ደረጃ መንፈስ ቅዱስን ይሹታል። እንደዚሁም ደግሞ ተጠራጣሪ ሰዎች፣ የቡድሃ፣ የሂንዱና የእስልምና እምነት ተከታዮች ሁሉ ይፈልጉታል።

በበዓለ ሃምሣ ቀን መንፈስ በወረደ ጊዜ፤ ጴጥሮስ በዚያ ለተሰበሰቡት ህዝብ እንዲህ አላቸው፤ "ንስሃ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።



የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፤ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።"

በመቀጠልም፤ ጴጥሮስ የኢየሱስ መንግሥት ተከታዮች ለሆኑት በጻፈው በሁለተኛ መልዕክቱ ውስጥ እንዲህ ብሏል፤ "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል። የሰው ዘር ባመጸ ጊዜ ሰዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን አጥተዋል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉም ሰው ከእርሱ ጋር እንዲታረቅና በገዢው እንዲሞላ ይፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች የገዢውን እውቀት ለራሳቸው ለማከመቸት የሚፈልጉ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም የሰው ልጅ ነው። እርሱን ወደ ሕይወትህ መቀበልህ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተሻልክ አያደርግህም። የመንግሥቱ ሥልጣንና ኃይል ባለአደራ ያደርግሃል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም። "

ሌሎችም መንፈሱን እንዲቀበሉና በተለይም ደግሞ መንግሥቱ መላውን ምድር እንዲሞላ ልንፈልግ ይገባናል። ከመንግሥቱ ጋር ተስማምቶ የመኖርን ሕይወት የሚያመጣውን ኃይል መቀበል ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ችሮታ ነው፤ ምክንያቱም ንጉሡ ልጅ የሞተው ለሰው ልጆች ሁሉ ይህንን መብት ለመስጠት ነው። ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ፣ ስለአዲሱ መንግሥት ዜጎች በጻፈው የመጀመሪያ መልዕክቱ፤ "እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ" ሲል ጽፏል። ሌሎች ሰዎች በኢየሱስ በኩል ከአብ ጋር ስለሚኖራቸው ስምምነትና የአብን የተስፋ ቃል መንገር፤ ሌሎች ሰዎች ውድ የሆነውን የመንፈስን ስጦታ እንዲቀበሉ እድል ይሰጣቸዋል።

## ለመግዛት የታደለ ብቃት

በሦስተኛ ደረጃ፤ ግንኙነትን እንደገና መፍጠራችን በዙሪያችን ያለውን ዓለም ለመግዛት የታደለ ብቃት ይሰጠናል። ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለኃይል የሰጠነውን ትርጉም ልብ ይሏል። ኃይል ሁኔታዎችን የመግዛትና የመቆጣጠር ብቃት ነው። መንግሥታት እያደረጉ ያሉት ዋነኛ ነገር ይሔው ነው፤ የገዢውም ወደ ምድር መምጣት ለዚሁ ዓላማ ነው። .

በአንድ ቅኝ ግዛት ውስጥ የገዢው ተግባር የዚያችን ቅኝ ግዛት ሕይወት መግዛትና እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር ነበር። ከሰው ዘር የመጀመሪያው ዐመጽ ጀምሮ ዓለም እየተገዛችና በቁጥጥር ሥር ውላ ያለችው በጨለማው መንግሥት ነው፤ እናም እንደገና ሕይወት በምድር

ላይ ትክክለኛውን መስመር የሚይዘው በገዢው ኃይል በኩል ብቻ ነው። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ተከታዮች ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና። እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።" ገዢው ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ላይ ለመግዛት የሚያስፈልገንን የመንግሥቱን ሥልጣን ይሰጠናል፤ ይህም የንጉሡን ባህርይ ያንፀባርቃል።

## የውክልና ሥልጣንና የብቃት - ሥልጣን

ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ መወያየት እንደጀመርነው፤ ሁለት ዐይነት የመንግሥት ሥልጣኖች አሉ፤ (1) ህጋዊ ወይም የውክልና ሥልጣን እና (2) የብቃት - ሥልጣን ናቸው። አንደኛው አንድን ነገር ለመስራት መብት ይሰጥሃል። ሌላኛው ደግሞ ግዳጅህን ለማከናወን የሥልጣን ከለላና ኃይል እንዲሁም ብቃትን ይሰጥሃል።

ንጉሣዊ ገዢው በቅኝ ግዛት ውስጥ በንጉሡ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን አለው። በቱርክስና ካይኮስ ደሴቶች ንጉሣዊ ገዢ መኖሪያ ቤት በእንግድነት በተገኘሁበት ጊዜ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ንግሥቲቱ በቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ ንጉሣዊ ለመኖራቸው ብቸኛ አካላዊ ማረጋገጫ የሆኑት ገዢው ብቻ ነበሩ። ሆኖም ሁሉም ሰው በታላቅ አክብሮት ይንከባከባቸዋል፤ ይሰግዳል፣ እጃቸውን ይጨብጣል፤ ከቡርነትዎ እያለም ይጠራቸዋል። ለምን? ምክንያቱም በቱርክስና በካይኮስ እርሳቸው የእንግሊዝ አስተዳደር ስለነበሩ ነው። እርሳቸው ንጉሣዊ አገዛዝ ነበሩ። የእንግሊዝ መንግሥት የሥልጣን ከለላ አላቸው።

> የውክልና ሥልጣን ቢኖርህና የብቃት - ሥልጣን ባይኖርህ ብዙ ነገሮች ተከናውነው አታያቸውም

ንጉሣዊ ገዢ በቅኝ ግዛት ዘመን በተጨማሪ የብቃት - ሥልጣን ነበረው፤ ይህም ማለት ተግባሩን ያከናውን ዘንድ በንጉሡ ኃይል ተሰጥቶታል ማለት ነው። ገዢው የተሰጠውን ኃላፊነት ይወጣ ዘንድ ንጉሡ ሰዎችንና ቁሳቁሶችን በማቅረብ የብቃት - ሥልጣን ሰጥቶታል። በመሆኑም ገዢው፣ በመንግሥቱ ባሉ በሰውና በጥሬ ዕቃዎች ኃይል የታገዘ ነበር። ይህ ታላቅ ነጥብ ነው፤ ምክንያቱም የውክልና - ሥልጣን ቢኖርህና ነገር ግን የብቃት - ሥልጣን ባይኖርህ፤ ምናልባት ያን ያህል ብዙ ሥራዎች ተፈጽመው አታያቸውም። የመተግበር ኃይል ማለት ገዢው ምንም ነገር ቢፈልግ ንጉሡ ያቀርብለታል ማለት ነው። ለምሣሌ ያህል፤ ኢየሱስ በምድር



ይኖር በነበረበት ዘመን ጲላጦስ፣ በፍልስጤም እንደ ሮም መንግሥት ተጠሪነቱ፤ ሥልጣኑን የሚደግፉለት የሮም ወታደሮች ነበሩት።

እንዲሁ ደግሞ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ሰማያዊው ንጉሥ ከማንኛውም ለዋዊ ከሆነ ተቋም ወይም ኃይል ይልቅ የበለጠ ተሰሚነት ያለው ህጋዊ ሥልጣንና የብቃት - ሥልጣን ይሰጣል። ኢየሱስን በጲላጦስ ፊት ባቀረቡት ጊዜ፣ ሮማዊው ገዢ ኢየሱስን በሞት እንደሚቀጣው እንዲህ በማለት አስፈራራው፤ "ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።" ጲላጦስ ገዢ ነበር፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በውስጡ የሰማያዊ አስተዳደር ኃይል ተሞልቶ ንጉሥ እንደነበር አልተገነዘበም። ጲላጦስ ከነበረው ኃይል ይልቅ የማይወሰን (አለቅጥ) ኃይል ነበረው። ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ፣ ለጴጥሮስ ሊታደጉት የሚችሉ ዐስራ ሁለት ምድብ የንጉሥ ጠረኞች (የመላእክት ሠራዊት) መጥራት ይችል እንደነበር ነግሮታል። በመሆኑም ኢየሱስ ለጲላጦስ እንዲህ መልስ ሰጠው፤ "ከሰማያዊው አስተዳደር ሥልጣን ካልተሰጠህ በስተቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን የለህም። በምድር ላይ የሚያስፈልገኝን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ከመንግሥቴ ኃይል አለኝ። ይሁን እንጂ የእኔ ዓላማ ራሴን ነፃ ለማውጣት አይደለም፤ ይልቁንም በመስዋእትነቴ የሰውን ዘር ከአባት ጋር ለማስታረቅ ነው።" ይሰቀል ዘንድ በጲላጦስ እጅ ታልፎ መሰጠቱ በእርሱ ዘንድ ኃይል በመጥፋቱ አልነበረም፤ በምድር የመንግሥቱን ተልዕኮ እየፈጸመ ነበር።

ከትንሳኤው በኋላ፤ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው፣ እንደ ንጉሥ፣ ሰዎችን ከመንግሥቱ ጋር የማስማማት ተግባራቸውን እንዲወጡ የውክልና - ሥልጣንንና የብቃት - ሥልጣንን ሲሰጣቸው ኃይል እንዳለው ነው። ቃሎቹ በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ ተዘግበዋል፤

> ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር ነኝ።

በዚህ ስፍራ ስተጠቀምነው "ሥልጣን" ለሚለው ቃል የግሪክ አቻ ቃል፤ "ብቃት" እና "አንድን ነገር የማድረግ ኃይል" ማለት ነው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፣ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" ባለ ጊዜ፤ "ኃይል" ለሚለው ቃል የተሰጠው የግሪክ አቻ ቃል "ዱናሚስ" ነው። ይህም ማለት "ተአምራዊ ኃይል" "ኃይል"፣ "ጉልበት" እና "ጥንካሬ" ማለት ነው። ተከታዮቹ ሁሉ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ይወጡ ዘንድ የሰማይ መንግሥት ኃይል ይኖራቸዋል። ይህ የብቃት - ሥልጣን ወደ ሕይወታቸው የመጣው በበዓለ ሃምሣ ቀን ከገዢው መፍለስ ጋር ነበር።

ሉሲፈርና የጨለማው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ በሰማያዊው ንጉሥ ሲሸነፉ፤ በርግጥ "ዘፍጥረተ ሁለት" ይኖረናል። ንጉሡ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚኖሩ ቃል ገብቷል፤ በዚያም የሰማያዊውን መንግሥት ክብር ሙሉ ለሙሉ እናንጸባርቃለን። ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸው ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ቃሎች የተወሰዱ ስለ አዲሱ መንግሥት የሚያብራሩ መግለጫዎች ናቸው።

> ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።

> "አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፤ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፤ ታላቅም ድምጽ ከሰማይ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፣ እነርሱም ህዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከአይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ሀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲያ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፏልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።

## በሕይወት ላይ የተለወጠ አመለካከት

ዐራተኛ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በእውነት እየኖሩ አለመለወጥ በጭራሽ የማይቻል ነገር ነው። የሰው መንፈስ፣ ነፍስና አካል እንደገና በአግባቡ ተቀናጅተው የሚሠሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ምክንያቱም ማንም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ቢሆን እንደገና እውነተኛ ሰው ሆኗል።

ለምሳሌ ያህል፤ በአመለካከታችን ላይ ታላቅ የሆነ ለውጥ ይከሰታል። ቀደም ሲል እንዳየነው ከዐመጽ በፊት የአዳም እውቀት የመንፈሱ ባሪያ ነበር። ከዚያ በኋላ፤ መንፈሱ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሙት በሆነ ጊዜ፤ እውቀቱና ስሜቱ ስፍራውን በመያዛቸው ገዢዎች ሆኑ። ከንጉሡ ጋር ያልተለሰፉና መንፈሱንም ያልተቀበሉ ሁሉም የሰው ልጆች ራሳቸውን የሚያገኙት በዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው።

> በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በእውነት እየኖሩ አለመለወጥ በጭራሽ የማይቻል ነገር ነው።

ገዢው በአንድ ሰው ውስጥ ለመኖር በሚመጣበት ጊዜ፤ በዚህ ዓለም መንግሥት ተጽእኖ የተደረገበትን የዚያን ሰው የአመለካከት ቅኝት ፈጥኖ



ማጥቃት የሚጀምረው በዚህ ምክንያት ነው። እንደገናም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሰማያዊው መንግሥት ህገ መንግሥት ብለን ልንጠራው የምንችለው በማስጠንቀቂያ ቃላት የሚመከረን በዚህ ምክንያት ነው፤

> "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በእርሳቸው ይቃወማሉ።"

> "ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የስጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ"

> "የሰውንም ሃሣብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሣለን፤ ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን። "

እነኚህ መግለጫዎች ሁሉ የሚያመለክቱት በሰማያዊው መንግሥት የአመለካከት ቅኘትና በጨለማው መንግሥት የአመለካከት ቅኘት መካከል ያለውን የከረረ ግጭት ነው።

አመለካከታችን፤ የንጉሡን አስተሳሰብና መንገዶች በመረዳትና በመቀበል እንዲሁም ገዢው ለሕይወታችን የሚሰጠውን ትእዛዝና መመሪያ በመቀበል ሲለወጥ ይገባዋል። ሕይወትን በቀደመው የአመለካከት ቅኘታችን ልናስተናግዳት ብንሞክር፤ የመንግሥቱ የአስተሳሰብ ባህርይ ባልሆነ የቀደመ አመለካከት ላይ እንወድቃለን። ገዢው የንጉሡን መንገዶች እንዲያስተምረን እንፈልጋለን።

የምንኖርበትን አዲስ መንገድ በማስተማር ገዢው ውስጣዊ የአኗኗር ባህላችንን ይለውጠዋል። የንጉሡን አስተሳሰብና መንገዶች ይገልጥልናል፣ በመሆኑም እንረዳቸዋለን፣ እንከተላቸዋለንም። ንጉሡ እንዲህ ሲል የገለጸውን ልብ በሉ፤ "ሀሣቤ እንደ ሀሣባችሁ መንገዳችሁም እንደመንገዴ አይደለምና . . . ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ ሀሣቤም ከሀሣባችሁ ከፍ ያለ ነው"። በዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚለው ቃል "አውራ ጎዳናን" የሚያመለክት ሲሆን ይህም የሕይወትን ጉዞ ወይም የአተገባበር ስልትን አመልካች ሆኖ በተምሳሌት የቀረበ ነው። በሌላ አገላለጽ፤ ስለ ሕይወት ዘይቤ የሚናገር ነው። እናም ምድርን ለመግዛት ይረዳን ዘንድ የንጉሡን የመሰለ የሕይወት ዘይቤ እንዲኖረን ካስፈለገ የአመለካከት ቅኘታችንን ልንለውጥ ይገባናል። ከዚያ በኋላ እንደ ቀደመው የጨለማ መንግሥት አሮጌ ባህል ሳይሆን፤ እንደ ሰማያዊው መንግሥት አዲስ የሕይወት ባህል ለመኖር እንችላለን።

ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ፤ የአንድ ቅኝ ግዛት ዜጎች የተገዙለትን መንግሥት ታሪክ እንዴት እንዲማሩ እንደሚደረግ አውርተናል። በተመሣሣይ መንገድ ንጉሡ ከእርሱ መንግሥት ውጭ በነበርክበት ጊዜ የነበረውን የቀደመ ሕይወት እንድትረሣው ይፈልጋል። በሰማያዊው

መንግሥት ውስጥ የራስህን አዲስ ታሪክ እንድትገነባ ይሻል:: በሰው ትውልድ እና በግል ያለን ታሪክ የዐመጸኝነት፣ የውድቀት፣ የተዛባና ዓላማውን የሣተ የሞት ታሪክ ነው:: ነገር ግን በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ አዲስ በተወለድን ጊዜ ተቀባይነት ያለው (የመዋጀት) ታሪክ ያለን ሆነናል:: አሁን እንደገና ዓላማና አቅም ያለን ሆነናል:: ታሪካችን የሕይወት ያውም የዘላለም ሕይወት ታሪክ ነው:: ገዢውም ይህንን ታሪካችንን ያለማቋረጥ እንድናጠናው ያበረታታናል፤ በመሆኑም ከጳውሎስ ጋር፤ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏልና፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" ማለት እንችላለን::

ይህም ማለት ከቀደመው የኃጢአት ታሪካችን ሙሉ ለሙሉ የተለየ ትምህርት ልንማር ይጠበቅብናል ማለት ነው:: የዕብራውያን መጽሐፍ እንዲህ ሲል ይዘግባል፤ ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ:: ህጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ"፤ ካለ በኋላ እንዲህ ሲል ሌላ ሀሣብ ያክልበታል፤ "ዐመጻቸውንና ኃጢአታቸውንም ደግሞ አላስብም::" ንጉሡ እንዲህ ነው የሚለው፤ "ተመልከቱ፤ ኃጢአታችሁ ተወግዷል:: ከጨለማው መንግሥት እንዳመለጣችሁ በእውነት አስተውሉ::"

የመንግሥቱ ታሪክ የሆነው "ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሆነው ደስታ" ያንተ ነው:: ሉሲፈር "አንተ ኃጢአተኛ ነህ" እያለ በከሰሰህ ጊዜ ሁሉ፤ "በንጉሡ ልጅ ደም ተቤዥቻለሁ:: ኃጢአቴን ሁሉ አንጽቶታል፣ አጥቦም አስወግዶታል" ብለህ ልትመልስለት ትችላለህ::

የዕብራውያን መጽሐፍ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ "ከክፉ ህሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውሃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ:: ልባችን እንኳ በነፃ አውጪአችን ደም ነጽቷል:: በተጨማሪም አንድ ሰው ያለፈ ታሪክህን ቢያነሳብህ፤ "እያወራህ ያለኸው ስለሞተ ሰው ነው:: በአዲስ ሕይወት ልመላለስ ከሞት ተነስቻለሁ" ልትለው ትችላለህ:: በመሆኑም ገዢው የራስህ የሆነውን አዲሱን የመንግሥቱን ታሪክ ያስተምርሃል፤ ንጉሡ ለአንተ ያለው ፈቃድ ይህ ነው::

ጳውሎስም እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ::" በዐመጽ፣ በወንጀል፣ ፀድብርት፣ በፍርሃት፣ በግራ መጋባትና በጭንቀት ከተሞላ የአመለካከት ቅኝት ነጻ ወጥተን በጽድቅ፣ በሰላምና በመንፈስ ቅዱስ ደስታ በተሞላ ሕይወት ለመመላለስ አዕምሯችን መለወጥ ያስፈልገዋል::

ገዢው በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት መገኘትና ባህርይ መሆኑን አስተውሉ:: ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስን የተቀበላችሁ ከሆነ፤ ኢየሱስ እንዳደረገው፤ "እኔን ያየ አብን አይቷል" ለማለት የምትችሉ



ትሆናላችሁ:: ወደ ገዢው ባህል ስለመሸጋገራችን በይበልጥ ዘርዘር አድርገን በምዕራፍ ዐሥራ አንድ ላይ የምንመለከተው ይሆናል::

## አዲስ ጀግንነትና በራስ መተማመን

የኢየሱስ ደቀመዝሙር የሆነው ዮሐንስ፤ ከዋናው መምህሩ ከኢየሱስ የተማረውን ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንግስቱ ዜጎች እንዲህ ሲል አስተምሯል፤ "ልጆቼ ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ፤ አሸንፋችኋልም (የጨለማውን መንግሥት)፤ በዓለም ካለው ይልቅ (ሉሲፈርና ተከታዮቹ) ይቂቅ በእናንተ ያለው (ገዢው) ታላቅ ነውና::" መንፈሱ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፤ መንግሥተ ሰማይ አገር ቤታችሁ ይሆናል፤ የመንግሥቱም ሥልጣንና ኃይል ይኖራችኋል:: ከንጉሡ የላቀ ኃይልና አቅርቦት (ሀብት) ያለው በዚህ ዓለም ላይ ምንም ነገር ወይም ማንም የለም:: በመሆኑም፤ በምድር ላይ ሲያስፈራራህ ወይም ሲያጠቃህ በሚሞክር በማናቸውም ነገር "እጠፋለሁ" ብለህ ልትሰጋ አይገባህም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ኢየሱስ ያስተማረውን ባለመድኃኒቱ ሉቃስ እንዲህ ሲል ይዘግበዋል፤

ለእናንተ ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፤ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳን የሚበልጥ ሲያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ:: እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ:: አዎን እላችኋለሁ አርሱን ፍሩ:: አምስት ድንቢጦች በዐስር ሣንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም:: ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቆጠረ ነው:: እንግዲያስ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ:: እላችሁማለሁ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል::

ሰውን መፍራት በመንግሥተ ሰማይ ዜግነታችን ላይ እንደተጠመደ መጥመድ ነው፤ ምክንያቱም ከመንግሥቱ የአመለካከት ቅኝትና ደረጃ ውጭ እንድንኖር ያደርገናል:: ስንፈራ በስልጣንና በኃይል ነገሮችን ልንተገብር አንችልም፤ ይልቁንም በስጋትና በፍርሃት እናደርጋቸዋለን:: ጳውሎስ "ንጉሡ የሰጠን የፍርሃትን መንፈስ ሳይሆን፤ የፍቅርን፣ የኃይልንና ራስን የመግዛት መንፈስ" እንደሆነ ጽፏል:: በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሳንናወጥ ፀንተን መቆም እንችላለን፤ ምክንያቱም በገዢው ህልውና በኩል ንጉሡ በእኛ ውስጥ እንደሚኖር እናውቃለን::

> መንፈሱ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፤ መንግሥተ ሰማይ አገር ቤታችሁ ይሆናል፤ የመንግሥቱም ኃይል ይኖራችኋል::

## ከሕይወት ዓላማ ጋር እንደገና መገናኘት

ገዢው በአንድ ሰው ውስጥ ለመኖር ሲመጣ፤ ያ ሰው ከተፈጠረለት የሕይወት ተልዕኮ ጋር እንዲገናኝ ይረዳዋል፡፡ ነቢዩ ኢዮኤል ሽማግሌዎች ህልም እንደሚያልሙ፣ ጎልማሶች ራዕይ እንደሚያዩ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የንጉሡን ፈቃድ እንደሚተነብዩ ይናገራል፡፡ እኔ ለህልም የምሰጠው ትርጉም ወደፊት ሊከናወን ልታዩት የምትችሉት አንድ ነገር እንደሆነ ነው፡፡ ምናልባትም እናንተ ሙሉ ለሙሉ ሲፈጸም በሕይወት ኖራችሁ ላታዩት እንኳን ትችላላችሁ፡፡ ራዕይ ግን ልታደርጉት የምታዩት ነገር ነው፤ በሕይወት ዘመናችሁ ልታጠናቅቁ የምትችሉትም ነው፡፡

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን"፡፡ ገዢው በእኛ ውስጥ ሊኖር በመጣ ጊዜ አዲስ ፍጥረት ሆነናል፡፡ በመሆኑም ገና ከመፈጠራችን በፊት እንኳን ንጉሡ እንተገብረው ዘንድ ለእኛ ያቀደውን መልካም ሥራ በመንግሥቱ ውስጥ ለመሥራት መጀመር እንችላለን፡፡ ገዢው፤ ሽማግሌዎች እጥተናል ብለው ያሰቡትን ለመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን ህልም እንደገና ይሰጣቸዋል፡፡ ለጎልማሶች ደግሞ በማይረባ ነገር ላይ ጊዜያቸውንና ኃይላቸውን እንዳያባክኑ ይረዳቸው ዘንድ ራዕይን ይሰጣቸዋል፡፡ በተሰጡን የተለየዩ ስጦታዎቻችን አማካይነት እኛን ሁላችንን ገዢዎች ያደርገናል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ገዢው በሕይወታቸው የሚኖርበትን ትርጉም ይስቱታል፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፣ እርሱ የመጣው "ደስ የሚል ስሜት" እንዲሰማቸው፤ ወይም የሰዎችን አትኩሮት ወደ እነርሱ ለመሣብ የሚችሉበትን ብቃት ሊሰጣቸው ይመስላቸዋል፡፡ ይልቅስ፣ እርሱ የመጣው እኛ ብቻ ልናከናውን የምንችለውን የአንድ ነገር ራዕይ ወይም ህልም ሊሰጠን ነው፤ ምክንያቱም ይህ ነገር በምድር ላይ እንድንሠራው ለኛ እርሱ የሰጠን የተለየ ሥራ ነው፡፡ ይህ የተለየ ሥራ ይተገበር ዘንድ ኃይልን ሊሰጠን መጣ፡፡

በተጨማሪም፤ ነጽታችሁና ገዢውንም ተቀብላችሁ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የመንግሥቱን ሕይወት ለመኖር ኃይልን ሊሰጣችሁ እንደሚፈልግ ላታውቁ ትችላላችሁ፡፡ ስለዚህም የተፈጠራችሁለትን ታላቅ ሥራ ለመስራት እንድትችሉ፣ ከመንግሥቱ ባህርይ ጋር ተጻራሪ የሆኑ ዝንባሌዎቻችሁንና መሻቶቻችሁን በመንፈሱ ሥልጣንና ኃይል አማካይነት ከማሽነፍ ይልቅ ዘወትር ከእነርሱ ጋር ስትታገሉ ጊዜያችሁን ሁሉ ታባክናላችሁ፡፡ ኃይሉ በእናንተ በኩል ስለሚሠራ ሕይወታችሁ በመንግሥቱ አገዛዝ ሥር ለመሆኑ ማስረጃ ማስየት (ማቅረብ) ትችላላችሁ፡፡ ገዢው የመጣው "ለሥራ" አስፈላጊ የሆነውን ኃይል ሊሰጣችሁ ነው፡፡ እርሱ በምድር ያለው በእናንተ ራዕይ ወይም ሕልም



አማካይነት ምድር ለሰማይ እንድትገዛ ለመጫን ወይም ተፅዕኖ ለማድረግ ነው፡፡

## ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር ተግባቦት

በመጨረሻ፤ ግን በጣም ከፍ ባለ መልኩ፤ የገዢው መመለስ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ተግባቦት መፍጠር የምንችልበትን ብቃት ይሰጠናል፡፡ የሰማዩን መንግሥት ወደ ምድር ለማምጣትና በእርሱም መግዛት የምንችለው ከንጉሡ ዘንድ ግልጽ መመሪያ ካገኘን ብቻ ነው፡፡ የአንድ መንግሥት የውክልና ሥልጣን በአግባቡ ሊሠራ የሚችለው፤ የንጉሡ ዓላማ፤ ፍቃድና መሻት የውክልና ሥልጣን ለተሰጠው አካል ሲተላለፍ ብቻ ነው፡፡

ንጉሡ ለምድር ያለው መሻት በገዢው በኩል ለምክትል ገዢዎቹ መተላለፍና በእነርሱም አማካይነት ተግባራዊ ሊሆን ያስፈልገዋል፡፡ ገዢው በሌለበት ወይም ከገዢው ጋር ያለው ተግባቦት ችላ በተባለ ጊዜ፤ የንጉሡ እገዛዝ በምድር ላይ አይኖርም (አይታሰብም)፡፡ አንዳንድ የአስተዳደሩ መገለጫዎች (መገኘቶች) ሊታዩ ይገባቸዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ የሰማያዊው መንግሥት ቁልፍ የሆነው ለስዚህ ነው፡፡ ገዢው በሰው ዘር አገዛዝ በኩል የእግዚአብሔር ሀሣብ የመገለጫ ወኪል ነው፡፡

## ወደ ንጉሡ መድረስ

እስኪ እሁን ደግሞ፤ ከንጉሡ ጋር ለሚኖረን ተግባቦት ገዢው እንዴት ወሳኝ እንደሆነ በምሳሌ ላብራራው፡፡ በባሃማስ በቅኝ ግዛቱ ዘመን፤ ማንኛውም ሰው፤ ደግሜ እላለሁ "ማንኛውም ሰው" የምክር ቤት አባል ቢሆን፣ የአገር ውስጥ ኮሚሽነሮች ወይም ጳጳሱ ቢሆኑ፣ ወደ እንግሊዝ ሄደው ንግሥቲቱን ለማየት ቢፈልጉ፤ በቅድሚያ በንጉሣዊው ገዢ በኩል ካልሄዱ በቀር በፍጹም ወደ ንግሥቲቱ ሊደርሱ አይችሉም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ለቅኝ ግዛቲቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጭምር ተመሳሳይ ነበር፡፡

ከንጉሥ እባት ጋር ባለን ግንኙነትም ቢሆን ተመሳሳይ የሆነ ሂደት ነው ተግባራዊ የሚሆነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በትምህርት ደረጃቸው፤ ወይም በባለጠግነታቸው ወይም ለድሆች ካደረጉት ታላቅ ነገር የተነሣ ወደ ሰማያዊው ዙፋን ለመቅረብ (ለመድረስ) እንደሚችሉ ያስባሉ፡፡ በእኛ ምትክ በመሞት መንገዱን በከፈተልን፣ በንጉሡ - ልጅ በኩል ካልሆነ፣ በእብ ፊት ልንናገርበትና ልንሰማበት በሚያስችለን በገዢው ኃይል በኩል ካላደረግን፤ በንጉሥ - እባት ዘንድ ለሚ (እድማጭ) ማግኘት አንችልም፡፡

በባሃማስ ወዳሉት ገዢ ዘንድ በመሄድ ንግሥቲቱን ለማየት ፍቃድ ስትጠይቁ፤ በዚያ ስለሚኖራችሁ ቆይታና ተግባር ለለማንነታችሁ ጭምር ገዢው መልዕክትን ወደ እንግሊዝ ያስተላልፋሉ፤ የናስሁ መንግሥት

ነገር ደግሞ አስፈላጊውን የመውጫ ፍቃድ ከሰጡ መግባት ትችላላችሁ:: እንደዚሁ ደግሞ፣ ንጉሡ - ልጅ የመግቢያውን ፈቃድ ከሰጣችሁና ጥያቄያችሁንና መሻታችሁን በገገርው በኩል ባላችሁ ግንኙነት ለማቅረብ የምትታመኑ ከሆነ፣ በሰማያዊው ቤተመንግሥት በውስጠኛው ክፍል ወዳለው ወደንጉሥ - አባት ዙፋን ችሎት በቀጥታ መሄድ ትችላላችሁ:: የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሀፊ እንዳጻፈው፣ "እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ::"

ጆን ኤፍ. ኬኔዲ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ጊዜ፣ ክብ ቅርጽ ባለው ቢሮአቸው ውስጥ ተቀምጠው ከሚኒስትሮቻቸው ጋር ስብሰባ ያደርጉ እንደነበር ሰምቻለሁ:: በዚያ ጊዜ በዓለም ውስጥ ስለነበረው እጅግ አደገኛ ሁኔታ ይወያዩ ነበር፣ ፀረ ካስትሮ የሆኑ ኃይላት በኩባ መንግሥት ላይ መጋቢት 17 1961 ባደረጉት ወረራ መነሻነት ኩባና የሶቪየት ህብረት የኒኩሊየር መሣሪያ ሊጠቀሙ ይችላሉ የሚል ስጋት አንዱ የውይይታቸው አጀንዳ ነበር:: በአስተዳደር ዘመናቸው ካደረጓቸው ጉባኤዎች ሁሉ ይህኛው እጅግ አሳሳቢ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገ ስብሰባ ነበር:: ታሪኩ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፣ የስብሰባው አዳራሽ ቢሮ በድንገት ተከፈተ፣ አንድ ትንሽ ልጅ በክፍሉ ውስጥ በሚኒስትሮቹ ዙሪያ እየሮጠ አዳራሹን አቋረጠና በፕሬዚዳንቱ ጭን ላይ በደረቱ ተኛ:: እነኛ እጅግ የተከበሩ የካቢኔ አባላት ሁሉ በድንገት ጸጥ አሉ:: ይህ ትንሽ ልጅ በዓለም ላይ እጅግ ኃያልና ተደማጭነት ወዳለው - ወደ አባቱ ቀና ብሎ ተመለከተና - "አባባ፣ እነኚህ ሰዎች እነማን ናቸው?" ሲል ጠየቀ:: ፕሬዚዳንቱም፣ "ልጄ፣ እነኝህ ሚኒስትሮቼ ናቸው" ሲሉ መለሱለት፣ ልጁም በክፍሉ ያሉትን ኃያል ሰዎችን ከተመለከተ በኋላ ወደ አባቱ በጣቱ እያመለከተ፣ "ይህ የእኔ አባት ነው" አለ:: በዚያ ጊዜ ውስጥ ፕሬዚዳንቱ ከነማን ጋር ለስብሰባ መቀመጣቸው ቁም ነገር ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አልነበረም:: ልጁ ለአባቱ ፍፁማዊ የሆነ ቅርበት ስላለው ለማነጋገር ሙሉ መብት ነበረው:: ከንጉሥ - አባታችን ጋር ያለን ግንኙነትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው::

> የሰማዩን መንግሥት ወደ ምድር ለማምጣት የምንችለው ከንጉሡ ዘንድ ግልጽ መመሪያ ካገኘን ብቻ ነው::

## የንጉሡን ፈቃድ መስማት

ንጉሡ ዜጎቹን ሊገናኝ በፈለገ ጊዜ፣ ገገርው በዚህ ሂደት ተሳትፎአል:: ለምሳሌ፣ በማንኛውም ጊዜ የእንግሊዝ ንግሥት ለጉብኝት ወደ ባሃማስ ስትመጣ፣ ወደ ባሃማስ እንደምትመጣ ራሰዋ በቀጥታ ለሕዝቡ አታሳውቅም:: እርስዋ ለንጉሣዊ ገገርው ትነግራለች፣ እርሱ ደግሞ ለሕዝቡ ይናገራል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በማንኛውም ጊዜ ሰማያዊው ንጉሥ ምንም ነገር በምድር ላይ ለማድረግ ሲፈልግ፣ ለኛ በሚገልጽልን በገገርው በኩል ያደርጋል:: ጳውሎስ እንደ ጸፈው፣ "በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም::" በሕይወታችን የገገርው መገኘት፣ ንጉሡ ለኛ ያለውን ፈቃድ እንድንሰማና እንድናውቅ ያስችለናል::

ከንጉሡ መስማት ማለት በእውነቱ ለመንግሥቱ ዜጎች ተገቢ የሆነ ጉዳይ ነው፣ ለዚህ ጉዳይ ኢየሱስ አርአያ እንደሆነልንም ተቀምጦልናል:: አዲስ ኪዳን እንደሚነግረን፣ ኢየሱስ ሁልጊዜ የንጉሥ- አባቱን መመሪያ ለመስማት ከደቀመዛሙርት ተለይቶ ብቻውን ይሆን ነበር:: የአስተዳደሩን ሥራ ለማከናወን ፀሎት የርሱ ብቸኛ መንገድ ነበር:: በእውነቱ እርሱን በትክክል ለመወከል፣ ከሰማያዊ አስተዳደር መመሪያዎችን ለመቀበል መቻል ያስፈልጋል:: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፣ "ስትፀልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ ... አንተ ግን ስትፀልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ፀልይ" አላቸው:: ስለዚህ፣ ፀሎት የምርጫ ጉዳይ አይደለም፣ ነገር ግን የየዕለት አስተዳደራዊ ተግባቦት (ግንኙነት) ነው:: በገገርው እርዳታ ንጉሡን ልንጠይቀው ይገባል፣ "ዛሬ ምን እንዲደረግ ትፈልጋለህ?" ብለን መጠየቅ አለብን:: እናም ለማዳመጥና ለመመለስ መዘጋጀት አለብን::

## ትክክለኛ በሆነ ግንኙነት (ዝምድና) ውስጥ መቆየት

ንጉሡን ማምለክ ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር የሚደረግ የተግባቦት ሌላኛው መልክ ነው:: ብዙ ሰዎች የአምልኮ ሥርዓት ያደርጋሉ፣ ሥርዓቱ ከንጉሡ ጋር ያለው ትክክለኛ ግንኙነት ተጠብቆ እንዲቆይ በመፈለግ ነው፣ በርግጥ ይህ ከበላይ ገገርአችን ጋር በማይቋረጥ ግንኙነትና ህብረት ለመቆየትና ለአስተዳደሩ ክብር ለመስጠት እንድንችል የሚያደርግ መንገድ ነው::

አምልኮ በምድር ላይ፣ ከሰማያዊው አስተዳደር ውጭ፣ የየራሳችንን መንግሥት እንዳንመሠርት ይጠብቀናል፣ ምክንያቱም በአምልኳችን የእርሱ መሻትና ፈቃድ በሕይወታችን የበላይ መሆኑን እውቅና እንሰጣለን፣ እናረጋግጣለንም:: አሁን በምድር ላይ የምንኖርበት የመጨረሻው ምክንያት የአስተዳደሩ ፍላጎት መሆኑን እናረጋግጣለን::

በገገርው በኩል ከመንግሥቱ ጋር የመገናኘት አስፈላጊነት በሚቀጥሉት ምዕራፎች የመንፈስ ቅዱስን ባህርይና ሚና እንዲሁም በየግል ሕይወታችን ባህልና በጥቅሉም በምድር ባለው ባህል ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ሰንቃኝ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል::

# ክፍል ሦስት

## ገዢውን ማወቅ



# ምዕራፍ ዐስር

## የገዢው ባህርይ

*ለራሱ (ብቻውን) የተተወ ሰው የራሱ አጥፊ ይሆናል።*

ዓለምን ወደ ሰማያዊው *መንግሥት ለመለወጥ* የገዢው *መኖር* እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አይተናል። አሁን ደግሞ *የመንፈስ* ቅዱስን ባህርይ በጥልቀት ልንመለከት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ምንም እንኳን ገዢው በምድር ላይ ከሁሉ በላይ ቢሆንም፣ ሰዎች ደግሞ ከሁሉ ነገር በላይ ያልተገነዘቡትና ቸልም ያሉት እርሱኑ ነው።

እስከ እሁንም ድረስ ወደ *መንግሥቱ* ያልገቡ ሰዎች፤ *መንፈስ* ቅዱስ በሕይወታቸው ውስጥ ሊጫወተው የሚገባው ሚና እጅግ ወሳኝ እንደሆነ አይገነዘቡትም፤ ምክንያቱም እርሱ ሚስጥራዊና ሊታወቅ የማይችል ነው ወደሚል ድምዳሜ አምርተዋል። ወይም ደግሞ እርሱ የሆነ ዐይነት *መንፈስ* እንደሆነ ያስባሉ፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ "*መንፈስ*" ለሚለው ቃል በዚህ *ዘመን* የሰጠነው ማብራሪያና በኪንግ ጄምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ውስጥ "*መንፈስ* ቅዱስ" ለሚሰው ቃል የተሰጠው "Holy Ghost" የሚለው ቃል ነው። ገዢውን በሕይወታቸው የተቀበሉ ሰዎች እንኳን ስለማንነቱ የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት አንዳንዶች እርሱ (*መንፈስ* ቅዱስ) ዓላማው እነርሱ ደስ እንዲላቸው የሚያደርግ ስሜት ወይም አነቃቂ እንደሆነ ያስባሉ። እስኪ ገዢው ያልሆናቸውን (እንዲህ አይደለም የምንላቸውን) በመዘርዘር ባሕርዩን እንቃኝ።

### መንፈስ ቅዱስ ያልሆነው

ሰብእና የሌለው "ነገር" (IT) አይደለም።

*መንፈስ* ቅዱስ "ነገር" ወይም "ዕቃ" አይደለም። እንዳንድ ሰዎች ሰብዕና የሌለው ዕቃ አድርገው ስለሚቆጥሩት፤ "ይሰማሃል?" ወይም "እርሱ እለህን?" ሲሉ ይደመጣሉ። *መንፈስ* ቅዱስ ሰብእና ያለው (ሰውነት) ነው። በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ስለ እርሱ የሰብእና ባህርያት በዝርዝር እንወያያለን።

## መንፈስ ቅዱስ

### ግዝፈ ዓበማዊ "ኃይል" ወይም "ከመረዳት የሚያልፍ አዕምሮ" አይደለም

መንፈስ ቅዱስ፤ በተጨማሪ፣ ስለ ግዝፈ ዓለም እውቀት ይኖረን ዘንድ የምንቀበለውና "ጠልቀን የምንገባበት" የሆነ ዐይነት ኃይል ወይም ከመረዳት የሚያልፍ አዕምሮ አይደለም:: እርሱ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ንቃተ ሀሊና ድምርም አይደለም:: ለአንዳንድ ሰዎች፣ እነዚህ ፍልስፍናዊ ሀሣቦች፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር አንድ ሆነውባቸዋል:: ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስን ማንም ሊቆጣጠረው አይችልም፣ ወይም ማንም እውቀቱንም ይሁን ኃይሉን ሊይዘው አይቻለውም:: የእኛ ንቃተ ሀሊና አካልም አይደለም:: ከንጉሡ ጋር ግንኙነት በሚኖረንና ስመንግሥቱም ፈቃድ ራሳችንን አሳልፈን በሰጠን ጊዜ እውቀትንና ኃይልን የሚሰጠን የተለየ ሀልውና ነው:: እንዲሁ ዝም ብለን ከመፈለግና ከመቀበል ይልቅ በሕይወታችን የመንግሥቱን ዓላማ ለማራመድና እኛን እንደ ንጉሡ ልጆች ለማጠናከር ለሚሠራው ኃይሉ አመስጋኞች መሆን አለብን::

## መንፈስ ቅዱስ

### ደመና ወይም ጭጋግ አይደለም

አንዳንድ ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲያስቡ፤ ጭስ፣ ወይም ጭጋግ አስበስዚያም ደመና ሆኖ ወደ አንድ ስፍራ የሚመጣ እና አንዳንድ ጊዜም ሰዎች በወለል (በመሬት) ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ይመስላቸዋል:: ይህን ስል ግን መንፈስ ቅዱስ በሀልውና በመገኘት ወይም ሊታይ በሚችል መንገድ የሚገልጥባቸው እውነተኛ ጊዜዎች የሉም እያልኩ አይደለም:: ይሁን እንጂ ሁልጊዜም እነኝህን መገለጫዎች የሚፈልጉ ሰዎች ስግምታዊነትና ስፈጠራ የተጋለጡ እንደሆኑ አምናለሁ::

ኢየሱስ መንፈስን በጣም ቀላል ከሆነ ጭጋግ ጋር ከማመሳሰል ይልቅ፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "እርሱ" የሚል ቃል ነው የተጠቀመው፤

> "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል:: የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ሁሉ ይነግራችኋል:: እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና::"

ኢየሱስ "መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ" ማለት ይችል ነበር:: ይሁን እንጂ "እርሱ" የሚለውን ቃል በመደጋገም ተናግሯል፤ በዚህም መንፈስ



ቅዱስ የሆነ 'ኃይል' ወይም 'ደመና' እንዳልሆነ እርግጠኞች እንድንሆን የፈለገ ይመስላል::

## መንፈስ ቅዱስ

### ስሜት ወይም ግንዛቤ አይደለም

እንደገናም፣ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ስሜት አይደለም:: እንደሚመስለኝ የዚህ ችግር ከፊል ምክንያት፣ ወደ ህብረት አምልኮ የሚመጡ አንዳንድ ሰዎች ስለሕይወታቸው ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ በውስጣቸው ጭንቀት አለ:: ይሁን እንጂ ምቹ ሁኔታ ውስጥ መግባት እንደሚችሉ ስለሚሰማቸው እየጮሁ ዙሪያውን ይሮጣሉ:: በመሬት ላይ ይንከባለላሉ፣ እና ይህንን መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ:: በቃ ዝም ብለው ውጥረትን ነው የሚለቁት::

የመንፈስ ቅዱስን ነገር ለመለማመድ ድምፅ ማለማት አያስፈልጋችሁም:: ከፍተኛ ድምጽ የሚሰጡ ከበሮዎች፤ የቃጭሎች ጩኸት፣ ሁከትና ጭብጨባም አያስፈልገንም:: መጽሐፍ ቅዱስን ጠጥንቃቂ ብታነቡ፣ አብዛኛውን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የገለጠው በፀጥታ ውስጥ እንጂ በስሜት ውስጥ አልነበረም:: ነቢዩ ኤልያስ እንዲህ ዐይነት ልምምድ ነበረው፤

> "እነሆም እግዚአብሔር አለፈ፣ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅና ብርቱ ንፋስ ተራሮችን ሰነጠቀ፤ ዐለቶችንም ሰባበረ፤ እግዚአብሔር ግን በንፋሱ ውስጥ አልነበረም:: ከንፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም:: ከምድር መናወጥ በኋላ እሣት ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳት ውስጥ አልነበረም:: ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምጽ ሆነ:: ኤልያስ ያንን በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጎናጸፊያው ሸፈነ፤ ወጥቶም በዋሻው ደጃፍ ላይ ቆመ:: እነሆ ኤልያስ ሆይ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል ድምጽ ወደ እርሱ መጣ::"

ይሁን እንጂ ይህን ቃል ለመጨመር እፈልጋለሁ፤ መንፈስ ቅዱስ ስሜት አይደለም፤ ነገር ግን በእርሱ መገኘት ሰላሙን፣ ደስታውንና መጽናናቱን ስትለማመዱ ያለ ምንም ጥርጥር በስሜታችሁ ላይ ተጽእኖን ያሳድራል::

# መንፈስ ቅዱስ ማነው?

## መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መለፋፋት ነው

ስለ መንፈስ ቅዱስ ባህርይ ማወቅ ያለብን ትልቁ ነገር እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር መስፋፋት የሚለውን ሀረግ መጠቀም እወዳለሁ። እርሱ ወደ ሰው እና ወይም ሁኔታ፣ የመንግሥቱን ዓላማና ፈቃድ በግለሰቡ ሕይወት ወይም ሁኔታ ውስጥ ለማድረግ የተዘረጋ እግዚአብሔር ነው።

## ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው

ቀደም ሲል፣ ኢየሱስ ምንም እንኳን ፍጹም ሰው ቢሆንም ፍጹም አምላክ ስለሆነበት እውነታ ተነጋግረናል። እግዚአብሔር ወልድ በዓለም ውስጥ ሲተገብር ያለውን የመቤዠት ዓላማ ይፈጽም ዘንድ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆነ። እነዚህን በአንድ ጊዜ ሁለት ባህርያት የመልበሱ እውነታ ከአብ ጋር ያለውን አንድነትና እኩልነት ፈጽሞ አላጠፋውም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ፣ "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም። ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ" ሲል ይናገራል።

አስቀድሞ ያለህን ነገር እንደገና ለመያዝ አትሞክርም። ኢየሱስ፣ ምንም እንኳን በስብእናውና በተግባሩ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልዩ ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የተላከው በመንፈስ በኩል ነበር። ከሰማይ የተላከው መልዕክተኛ ለማርያም፣ ለኢየሱስ እናት፣ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሲል ተናግሯል። ኢየሱስም ከአብ ጋር አንድ ስለመሆኑ፤ "እኔና አብ አንድ ነን" እና፤ "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን" ሲል ተናግሯል።

> **መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ነው**

"አባት" ብለን ከእግዚአብሔር ጋር እያይዘን የምንናገርበት ቃል ለዋዊ ከሆነው አባት ጋር ወይም ለአንድ "ትልቅ" ወይም "በእድሜ ለገፋ" ሰው ከምንጠቀምበት ቃል ጋር ግንኙነት ያለው አይደለም። እግዚአብሔር



ከኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ "በእድሜ የገፋ" አይደለም። እግዚአብሔር አባት ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ዘላለማዊ ነው። ይልቁንም "አባት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተላከበት ምንጭ እንደሆነ ያመለክታል።

እንደዚሁ ሁሉ፤ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ነው። ዮሐንስ በወንጌሉ፤ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል" ሲል ጽፏል። ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፤ "ሌላ አጽናኝ" ይለዋል፤ እርሱም ኢየሱስ በምድር የጀመረውን ሥራ የሚቀጥል ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ይሁን እንጂ ራሱን በሶስት የተለያዩ ስብእናዎችና አሠራሮች ይገልጻል።

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፤ እርሱም ከአብ የሚመጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ . . . " ኢየሱስም ሆነ መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም በምድር ላይ መሠራት የነበረበትንና አሁንም የሚያስፈልገውን ሥራ ለማከናወን የወጡት ከአብ ዘንድ ነው። ኢየሱስ ይቤዠን ዘንድ ከአብ ተላከ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኃይልን ያስብስን ዘንድ በኢየሱስ ተላከ። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ግንኙነት እንደገና ሊያድስ ተላከ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አዲስ ወደሆነ ወደ መንግሥቱ ሕይወት ሊያስገባን ተላከ።

የሥላሴ አምላክን ጽንሰ ሀሣብ በውሃ ምሳሌ ውስጥ ልገልጠው እወዳለሁ። በፈሣሽ መልክ ያለው ውሃ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ ነው፤ እርሱ ምንጭ ወይም መነሻ ነው። ጥቂት ውሃ ወስዳችሁ ብታቀዘቅዙት ጥጥር በረዶ ይሆናል። በረዶው በኢየሱስ ይመሰላል፤ ሰጋ የሆነው ቃል፤ እርሱ የሚጨበጥ ነበር፤ ሊታይና ሊዳሰስም የሚችል ነበር፣ የሚሰማና የሚነካ ነበር። ያንኑ በረዶ ወስዳችሁ ደግሞ በሆነ ማሰሮ ውስጥ ክተቱና እስኪተን ድረስ አሙቁት፤ ወደ ተንነት ይለወጣል። ተን (እንፋሎቱ) እንደ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ተጽእኖ ማምጣት የሚችልን ኃይል የሚያመነጭ፤ ነገር ግን ሊታይ የማይችል ነው። በረዶም ይሁን ተን አስቀድሞ ወደነበሩበት ወደ ፈሳሽነት መለወጥ ይችላሉ። ሦስቱም የውሃነቱ ባህርይ ያላቸው ናቸው፤ ይሁን እንጂ በተለያዩ ገጽታዎች ይገለጣሉ።

## እንደ እግዚአብሔር ያለ ክብር ይቀበላል

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለመሆኑ ሌላው ማረጋገጫ፤ እርሱን መሳደብ ስለሚያስከትለው ውጤት ኢየሱስ የተናገረው ቃል ነው። "እውነት እላችኋለሁ፣ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ፤ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።" ኢየሱስ

ፈጽሞ ምህረት የማይገኝበት ብቸኛው ኃጢአት እንደሆነ የተናገረው፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሠራን ሃጢአት ነው። ይህንን ያለው ለምን ነበር? ይህንን የተናገረበት ምክንያት (1) ሰዎች በኢየሱስ ስራ ከኃጢአታቸው መንጻት እንደሚያስፈልጋቸው ሰዎችን የሚወቅስ በመሆኑና (2) በመንፈስ እንድንወለድ የሚያስችለን እንዲሁም ወደ ሰማያዊው መንግሥት የሚያመጣን እርሱ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ እምናለሁ። በመሆኑም አንድ ሰው ሙሉ ለሙሉ ለመንፈሱና ለስራውም ልቡን የሚያጠነክር ከሆነ፤ በክርስቶስ በኩል ወደሚገኘው ምህረት ሊቀርብ አይችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አንጽቶናል፣ አብ ይቅር ብሎናል፣ መንፈሱ ደግሞ አድሶናል። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ፤ ከመዝሙር ምዕራፍ 95 ጠቅሶ እንዲህ ጽፏል፤ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፦ ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ"። በሌላ አባባል፤ ድምጹን ብትሰሙ፣ ወቀሳውን ብታደምጡ፤ "ጊዜው አሁን ነው" ሲል ብትሰሙ፤ ልባችሁን አታጠንክሩ፤ ምክንያቱም እናንተን መጣራት የሚያቆምበት ቀን ይመጣል ማለቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለረዥም ጊዜ እንደሚታገስ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ እስከ "ለዘላለሙ" ይታገሳል አይለንም። ሞኝነትን ለረዥም ጊዜ ይፈቅዳል፣ ነገር ግን ለረዥም ጊዜ ብቻ።

"ሃይማኖቱን የከዳ ሰው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መንፈስ ለማድመጥ ጨርሶ ወደ ማይችልበት ሁኔታ ውስጥ የገባን ሰው ነው። መንፈስ ቅዱስ አንተን መውቀሱን እንዲያቆም አትፈልግም። መንፈስ ቅዱስ ንስሃ መግባት እንዳለብህ፣ ምህረትን እንድትቀበልና ወደ መንግሥቱ እንድትገባ ሲወቅስህ ፈጥነህ ወደ እርሱ መሮጥ ይገባሃል! ለምን? ምክንያቱም ያ ማለት አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር በመልካም ግንኙነት ውስጥ አለህ፣ አንተን ሊያናግርህ ይችላል ማለት ነው። ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን? እያልክ እያሰብክ፤ የክብርህ ጉዳይ ምላሽ ከመስጠት እንዳያግድህ ተጠንቀቅ። ይልቁን መጨነቅ ካለብህ ልትጨነቅበት የሚገባህ ነገር መንፈስ ቅዱስ አንተን መናገሩን እንዳያቆም ነው።

በሰማይና በምድርም ሁሉ እጅግ ከፍ ያለውን እንደምታደምጠው ተስፋ አደርጋለሁ። እርሱ ሊገመት ከሚችል በላይ፣ ብዙዎች ሊያዩዋቸው ተስፋ ከሚያደርጓቸው መላእክት ይልቅ ታላቅ ነው። መላእክት ለአስተዳደሩ የሚሠሩ ናቸው፤ እርሱ ግን አስተዳደሩ ነው።

> **መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይወቅሳል፤ ደግሞ በመንፈስ እንዲወለዱም ያስችላቸዋል።**



## መንፈስ ቅዱስ የተለየ ጠባይ፣ ችሎታና ፍቃድ ያለው አካል ነው

ቀደም ብለን እንዳየነው በመጀመሪያ ደረጃ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጫ ነው። ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ስብእና ነው። አንድ ስብዕና ከሌሎች ይልቅ ልዩ የሚያደርጉት የተለዩ ጠባዮችና ችሎታዎች ይኖሩታል፤ በመሆኑም እርሱ የተለየ ህልውና ነው፣ ገዢው የተለየ ስብእና፣ ጠባይና ፈቃድ አለው። ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ላይ፣ ሰማያዊ ወኪል ሆኖ የሚኖር ገዢ ዋንኛ ፍላጎቱ እኛ በምድር ላይ የንጉሡን ዓላማ እናደርግ ዘንድ ነው።

ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስብእናና ስለተግባሩም በመግለጥ እንደተናገረው፤ ከጠባዮቹ መካከል ሁለቱ የማስተማርና የመምራት ብቃቶቹ ናቸው። እርሱ "ስሜት" አይደለም። "ስሜት" ወይም "እንድ ኃይል" ገዢ ሊሆን አይችልም። "ጭጋግ" ሊያስተምር ወይም ሊመራ አይችልም። የመንግሥቱ ዜጎች የሆኑ ብዙ ሰዎች ከገዢው ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት የላቸውም፤ ምክንያቱም በእነርሱ ውስጥ እጅግ የከበረው እርሱ መኖሩን አልተገነዘቡም። የከበረው እርሱ።

## መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕዋሶች አሉት

መንፈስ ቅዱስ "ሕዋሶች" ደግሞ አሉት፣ እነርሱም የስብእናው አካል ናቸው። ይህም ማለት፣ ልክ የሰው ልጆች አካላዊ የሆኑ ሕዋሶች እንዳሏቸው፣ እርሱ ደግሞ መንፈሳዊ የሆኑ ሕዋሶች አሉት ማለቱ ነው። በመንፈሳዊ ሁኔታ ስንናገር፣ መንፈስ ቅዱስ ያያል፤ ይሰማል፤ ይዳስሳል፣ ያሸታል ወይም በምድርና በምድር ላይ ከሚኖሩት ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ነገሮችን ይረዳል ማለቱ ነው።

## መንፈስ ቅዱስ ስሜት ብቻ ሳይሆን ትልቅ ስሜት አለው

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" እርሱ የሚለንን ላለማድረግ እልከኞች ስንሆን፣ ሰማያዊውን መንግሥት በሚቃወም ሁኔታ ብንመላለስ ወይም እርሱን ችላ ብንለው ልናሳዝነው እንችላለን።

አሁን ማተኮር የምፈልገው እርሱን ችላ በምንልበት ሁኔታ ላይ ነው። እስኪ እንዲህ እስቡ፣ አንድን ሰው ችላ ብትሉት በአጠቃላይ ከእናንተ ጋር መነጋገሩን ያቆማል። በጣም ችላ እያላችሁት በሄዳችሁ መጠን እርሱም የዚያኑ ያህል ችላ ይላችኋል። ለምሳሌ እኔን ልትቀበሉኝ ፈቃደኞች ካልሆናችሁ፤ እኔ ለእናንተ ምንም ጠቀሜታ የሌለኝ ሰው እንደሆንኩና ለእኔ ምንም ፍላጎት የላችሁም ወደሚል ድምዳሜ አደርሳለሁ። ወይም ደግሞ እየተናገርኳችሁ ላለ ችላ ካላችሁኝ እነዚህ ሰዎች ሊሰሙኝ ፍላጎት የላቸውም ወደሚል ስሜት ሳዘነብል እችላለሁ። ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል" ብሎናል። እኔ

ሰዎች እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፣ "እማኝ" (የመንግሥቱ ዜጋ) ለመሆን እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን እኔ ለዚህ የሚያበቃ ጥንካሬ የለኝም። ይህን ላለማድረግ እና ያንን ለማድረግ በቂ ጥንካሬ ሲኖረኝ ያኔ መንግሥቱን እቀበላለሁ።" እነኝህ ሰዎች ዛሬም ውሳኔ አላደረጉም፣ ምክንያቱም በመጀመሪያ መጠንከር እንዳለባቸው ያስባሉ። ምናልባት አንተም ራስህን በራስህ መንገድ ለመለወጥ በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እየታገልክ ይሆናል። ንጉሡ እንዲህ ይለናል፣ "ተመልከት፣ የመንግሥቱን ባህል ለመማር የምትፈልግ ከሆነ፣ ከሰማይ (ከአገር ቤት) እርዳታ ያስፈልግሃል።" ገዢውን ወደ ሕይወትህ መቀበል እንድትለወጥ ያስችልሃል። አስተሳሰብህን እንዴት እንደምትለውጥና እንዴት እንደምትኖር መንገዱን ያሳይሃል።

እንደዚሁ ደግሞ፣ ምንም እንኳን የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች ብትሆኑም፣ አንዳንዶቻችሁ ተስፋ ቆርጣችኋል፣ ምክንያቱም ወደ ጨለማው መንግሥት ባህርያትና ተግባራት ተመልሳችሁ እንደምትወድቁ ይሰማችኋል። ገዢው ግን እንዲህ ይላችኋል፣ "እኔ እንደገና ፀንታችሁ እንድትቆሙ እረዳችኋለሁ።" ይህ የእርሱ ሥራ ነው፣ እርሱ ሥራውን በእናንተ ላይ አያቋርጥም።

ኢየሱስ፣ ዘጠና ዘጠኙን በጎች በሜዳ ትቶ የጠፋውን አንድ በግ ለመፈለግ በወጣው እረኛ ምሳሌ፣ ንጉሡ ለአንተ የሚያደርገውን ከፍተኛ ጥንቃቄ ገልጾልሃል። ይሄ ግን ተመልሰን ወደ ጨለማው መንግሥት ባህርያት እንድንሄድ ፈቃድ አይሰጠንም። አንድ ጊዜ በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ከገባን፣ ሆን ብለን በቀደመው አሮጌ መንገዳችን መመላለስ አይጠበቅብንም። አንዳንድ ሰዎች ሆን ብለው ከመንግሥቱ ባህርይ ተፃራሪ የሆነ ነገር ያደርጉና፣ ወዲያውኑ ደግሞ ንጉሡ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ይፈልጋሉ። ይህ የመንግሥቱ ዜጋ ሆነን በእውነት መለወጣችንን የሚያንፀባርቅ ነገር አይደለም። በርግጥ በሰማያዊው መንግሥት መስኪያ ለመኖር የምንሻ ከሆነ፣ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ብንሳሳትም፣ ገዢው በመስኪያው መሠረት እንድንኖር ይረዳናል። እርሱ ስኬታማዎች እንድንሆን ይፈልጋል።

## መሪና አስተማሪ

ኢየሱስ ስለ ገዢው እንዲህ ሲል ተናገረ፣

> "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፣ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል።"

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ገዢዎች በቅኝ ግዛት ውስጥ የሚቀመጡት መረጃ ለማስተላለፍ ብቻ አይደለም፣ ይልቁንም የግዛቲቱ ነዋሪዎች አስተሳሰባቸው፣ አደራረጋቸውና የአኗኗር ደረጃቸው በአገር ቤቱ



መስኪያ፣ ልማድና - ሁለንተናዊ ባህል መሠረት እንዲሆን ለማሠልጠን ነው። ይህ ደግሞ አጠቃላይ ትምህርትንና በየግል የሚሰጥ ሥልጠናን ይጨምራል።

ገዢው ልኡላዊ ከሆነው ዙፋን ወደ ቅኝ ግዛት የተላከ በመሆኑ፣ የልዑላዊውን (የበላዩን) ፍላጎት ያውቃል። በዚሁ ዓይነት መንገድ፣ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃሎችና ለእኛ የተወለንን መመሪያዎች እውነት ልንረዳ እንድንችል የሚያደርገን፣ ከሰማይ የሆነው ገዢ ብቻ ነው። ስለ ንጉሡና ስለመንግስቱም ዋና ወይም ትክክለኛ ወደ ሆነ መረጃ የሚያገናኘን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። እንደ ንጉሡ የልብ ሃሣብ ካልሆኑ ስህተት ከሆኑ ነገሮችና ከሌሎች ሰዎች አስተሳሰቦች ይጠብቀናል።

በቅኝ ግዛት ውስጥ ገዢ ከሚኖሩት ተግባራት መካከል አንደኛው፣ ሉአላዊው ለዜጎቹ ባስተላለፋቸው መመሪያዎች ወይም ቃሎች ምን ማለቱ እንደሆነ መተርጎም ነው። ባለፍነው ክፍል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ "መካር" ተብሎ ተጠርቶ አይተናል። "መካር" የሚለው ቃል ህግን ከመተርጎም ጋር ይያያዛል፣ በመሆኑም ገዢው የንጉሡን ቃሎች ወደ ሕይወታችን እያመጣ ሕጉን ያብራራልናልም።

ነቢዩ ኢሳያስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ - የጥበብና የማስተዋል የምክርም መንፈስ ያርፍበታል"። በእኛ ደግሞ ይህ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ በውስጣችን ይኖራል። እውቀት መረጃ ሲሆን ጥበብ ደግሞ እውቀት እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ ጥበብ እውቀትን አግባብ ባለው መልኩ መጠቀም ነው። ገዢው እውቀታችንን እንዴት እንደምናወጣና ለሕይወታችን እንዴት እንደምንተገብረው ያሳየናል። በዓለም ላይ ትክክለኛና ተግባራዊ የሆንን ሰዎች እንድንሆን የሚያስችለን እርሱ ነው። በአንዳንድ የሃይማኖት ክበባት፣ ይህ የሚታሰበው በተቃራኒው ነው። ሰዎች እንግዳ በሆነ መንገድ ነገሮችን እንዲተገብሩ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁን እንጂ እውቀታችንን በቤተሰባችን፣ በንግዳችን፣ በማህበረሰባችን ውስጥ፣ በሀገራችንና ዓለም ዓቀፋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደምንችል የሚያሳየን እርሱ ነው።

> ገዢው መንፈሳዊ ዕውቀትን
> ዘርፈ ብዙ ለሆኑ ለሕይወት
> ጉዳዮቻችን እንዴት
> እንደምንጠቀም ያሳየናል።

## ረዳትና አስቻይ

ንጉሡ ልጅ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ራሱን በሚመለከት ከነቢዮ ኢሣያስ መጽሐፍ ጠቅሶ እንዲህ አለ፣

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድውዮች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታስሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፤ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ፤ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል::"

ሉአላዊው ለቅኝ ግዛቱ የሚፈልገውን ነገር ሲያስታውቅ፤ ነገሩ እንዲከናወን ዜጐቹን ማበረታታትና መከናወኑንም ማረጋገጥ የገዢው ሥራ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ ሲፈጽም፣ በግዛቲቱ ላይ እንደ ምክትል ገዢነታችን ሚናችንን በመወጣት ለርሱ ዓላማና መሻቱ መተባበር ይጠበቅብናል:: እዚህ ያለነው "የየራሳችንን" መንግሥት ለመመስረት አይደለም:: በዚህ ያለነው የምንወክለውን ሉአላዊ መንግሥታችንን ለመመስረት ነው::

## የመንግስቱን ዓላማ በማሟላት ረገድ

ከዚህ በላይ ከኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ምንባብ በምድር ላይ ያለውን የመንግስቱን የትኩረት አቅጣጫ፣ ማለትም በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ስለ አብ የተስፋ ቃል በመንገር፣ ከጨለማው አገዛዝ ነጻ እያወጣቸው የመንግሥቱን ባህርይና እንዴት ወደርሱ እንደሚገቡበት እያሳያቸው ያብራራል:: እነኝህን ነገሮች ሁሉ ማከናወን እንድንችል የሚረዳን ገዢው ነው::

የንጉሡ የመጨረሻ ዓላማው በነቢዩ እንባቆም አፍ እንደተናገረው ነው፤ "ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለችና::" እንግዲህ መንግሥቱን በተመለከተ ይህንን ቃል እንደ መመሪያ አድርገን ልንወስደው እንችላለን:: በተጨማሪም፤ የእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርን ባህርይ ያመለክታል:: ኢየሱስ፣ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው፣ ደቀመዛሙቴ አድርጓቸው" ብሎ እንደተናገረው በገዢው ምሪት ሆነን መፈፀም አለብን:: ትንቢቱ የሚፈፀመውም በዚህ መንገድ ነው::

ገዢው የመንግሥቱን ባህል አሁን በምድር ላይ ወደሠለጠነው ወደ ጨለማው (ባዕድ) መንግሥት ባህል እንድናመጣው ይጠራናል:: ቀደም ሲል፤ ደቀመዝሙር ማድረግ ማለት የመንግሥቱን ፍልስፍናና እሴቶች ማስተማር እንደሆነና በዚህም ተማሪዎቹ በንጉሡ የአመለካከት ቅኝት ውስጥ እንደሚዘፈቁ ተመልክተናል:: "ዓለም" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "ኢትኖስ" ማለት ሲሆን የሚያመለክተውም ዘርን ወይም የሰዎችን ቡድኖች ነው:: የትኛውም በምድር ላይ ያለ የተለየ የሰዎች ቡድን ወደ መንግሥቱ ባህል ሊለወጥ ያስፈልገዋል::



የባሃማስ ንጉሣዊ ገዢ የነበሩት በቅኝ ግዛቲቱ ውስጥ የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮጀክቶችን፣ እንደ መንገዶችን የመጠገን ሥራ የመሳሰሉትን እንዲሠሩ ኮምሽነሮችንና የህዝብ አማካሪዎችን ከዚያቹ ቅኝ ግዛት በመወከል ይሾማቸው ነበር:: እንደዚሁ ሁሉ፣ ገዢው ለኛ በዓለም ውስጥ ሰማያዊ አስተዳደርን በመወከል መልካም ሥራ እንሠራ ዘንድ ሥልጣን ይሰጠናል:: ጳውሎስ እንደጻፈው፤ "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን::"

## ወደ ተሰጡን ስጦታዎች ምንጭ እንደገና በማገናኘት ረገድ

እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ከእግዚአብሔር ከተሰጡት ስጦታዎች ጋር ነው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ስጦታዎች ወደ ላቀ የብቃት ደረጃ ደርሰው ለመንግሥቱ አገልግሎት እንዲውሉ ከተፈለገ፣ ከዋናው ምንጫቸው ጋር እንደገና መገናኘት ይኖርባቸዋል:: ማንም ቢሆን ከፈጣሪው መንፈስ ጋር ካልተገናኘ በቀር፤ የስጦታውን እውነተኛ ባህርይ በትክክል አያውቀውም:: ከዚህም በላይ፣ ገዢው ስጦታዎቻችንን እኛ ልናመጣ (ልናሳድግ) ከምንችለው ደረጃ በላይ በማሳደግ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል:: ጳውሎስ፣ ነቢዮ ኢሣያስን በመጥቀስ እንዲህ ጽፏል፤ "ነገር ግን ዓይን ያላየችው፣ ጆሮም ያልሰማው፣ በሰውም ልብ ያልታሰበው፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ እንዲህ እንናገራለን:: መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና፤ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው::"

> ገዢው የመንግሥቱን ባህል ወደ ጨለማው ባህል እንድናመጣው ይጠራናል::

ገዢው ከስጦታዎችህ ምንጭ ጋር እንደገና የሚያገናኝህ በመሆኑ፤ የተሰጠህ ምን እንደሆነ ልትገነዘብ ትችላለህ፤ ይህም የስጦታዎችህን እሴት ብቻ ሳይሆን መጠናቸውንም እንድታውቅ ያደርግሃል:: በሌላ አገላለጽ፤ ማንኛውም ሰው ቢሆን በራሱ የአዕምሮ ችሎታ ብቻ፤ ንጉሡ ለመንግስቱ ዓላማ በውስጡ ያስቀመጠውን ስጦታ ሊለየውና ሊገነዘበው አይችልም:: ስለዚህም ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥህ ያስቀመጠልህ በርግጥ ምን እንደሆነ ለማወቅ ካስፈለገህ፤ ከገዢው ጋር መገናኘት የግድ የሚያስፈልግህ::

ጳውሎስ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፤ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ፤ የእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም::" ይሄ ቃል የሚነግረን፣ መንፈስ ቅዱስ ካልገለጠልን በስተቀር ያለን ምን እንደሆነ እንኳን ልንገነዘበው እንደማንችል ነው:: ይህ እውነት ዓላማህንና ያለህን እምቅ ችሎታ

ገዢ እንግሊዝ ውስጥ ከሚገኙት ንግሥት የተላከውን፣ "ከዙፋን የመጣ ንግግር" የተባለ ሰነድ ያነቡልናል። እያንዳንዱ ዜጋ ንግግሩን ለማዳመጡ እርግጠኛ ለመሆን ሲባል በመላው አገር በዓል ይሆናል፣ ሁሉም ነገር ይዘጋል።

ንጉሣዊው ገዢ በግዛቲቱ የአስተዳደር ባለሥልጣናት ተከበው በወንበሩ ላይ ይቀመጡና የእንግሊዝ ንግሥት ለቅኝ ግዛቲቱ የላኩትን ያነባሉ። ያ ንግግር ለአዲሱ ዓመት እቅድና ተግባራዊ ግዳጅ ይሆናል። ሉዓላዊው አገዛዝ ስመንግሥቱና ስቅኝ ግዛቲቱ ያለውን ፍላጐት እንድናስታውስ እንድንደረግና እንዲሁም ንግሥቲቱ ከቅኝ ግዛቲቱ የሚጠብቁት ነገር ምን እንደሆነ እንድናውቅ በአንድነት እንሰበሰብ ነበር። የንግግሩ ይዘት የመንግሥታቸው ህግ፣ ባህልና የሕይወት መስኪያ ቅኝት እና ለቅኝ ግዛቲቱም ያላቸውን የወደፊት እቅዶች የሚገልጹበት ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እርሱን ለማድመጥ ከሚያጨናንቅ የሕይወት ተግባር ራሳችንን አሳርፈን በፊቱ ስንቀርብ መንፈስ ቅዱስ ያስማቋረጥ ከሰማያዊው ዙፋን ንግግር ያቀርብልናል። የገዢው ቃል ከንጉሡ ቃል ጋር በጭራሽ የሚጣረስ አይደለም፣ ወይም ደግሞ እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ መልዕክቶችን አያመጣም። ንጉሡ አስቀድሞ የተናገረውን ነገር እና የሚፈልገውን ያስታውሰናል፣ በተጨማሪም የመንግሥቱን የወደፊት ሁኔታ በመተንበይ ይናገራል።

## ቀዳሽ

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፣

"እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ስመዳን እንደ በኩራት መርጧችኋልና።"

እንደ ቀዳሽነቱ፣ ገዢው ከንጉሡ ባህርይ ተፃራሪ ከሆኑት በሕይወታችን ካሉ ነገሮች ነፃ እንድንሆን ይረዳናል፣ ለመንግሥቱም ጠቀሜታ የሚውሉ ስጦታዎቻችን እንዳያድጉ እንቅፋት ከሚሆኑ ሁኔታዎች ነፃ ያደርገናል። ቀደም ሲል፣ መንጻት ወይም መቀደስ ማለት ሙሉ ስሙሉ መንጻትን እንዲሁም መስየትን የሚያመለክት እንደሆነ አይተናል። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ለእድገታችንና ለመሻሻላችን እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ያስወግዳቸዋል። ልክ ስንዴውን ከገለባው እንደመለየት ማለት ነው። ገለባው ለእኛ መልካም አይደለም። እርግጥ ነው መለየቱ በሚከናወንበት ጊዜ "የማበራየቱ ሂደት" የሚያሳምም ሊሆን ይችላል፣ ይሁን እንጂ ለጥቅማችን ነው። ንጉሡ ያለንን እምቅ ኃይል እንዳንጠቀምና ዓላማችንን ከግቡ እንዳናደርስ የሚያደርግ ማንኛውንም ነገር አይፈልግም።



እንዲሁም ገዢው፣ ለሰማያዊው መንግሥት አገልግሎት ይለየናል፣ ንጉሡ አዲስ በሚፈጠረው ምድርና አዲስ ሰማይ ከራሱ ህዝብ ጋር ስመኖር ለሚመለስባትም ቀን ይቀድሰናል። የእንግሊዝ ንግሥት በሃማስን ሊጎበኙ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ንጉሣዊው ገዢ ህዝቡ ሁሉ ለዚህ እንዲዘጋጅ መመሪያ ይሰጣሉ። መንገዶቹን መጥረግ፣ የአውራ ጎዳና መብራቶችን ማጽዳትና ዛፎችንና አበባዎችን መትከል የግድ ነበር። ንግሥቲቱ የማያዩት ቢሆንም እንኳን በመኖሪያ ግቢያችን ያሉትን ዛፎች እንከረክማለን። ለንጉሡ ዳግመኛ መምጣት፣ የሕይወታችንን የትኛውንም ዘርፍ የማዘጋጀት ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ነው።

በመሆኑም ገዢው እንደ ባህርው ሊቀርጸን የሚጠቀምባቸው ዋንኛ መንገዶች እነዚህ ናቸው። በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ገዢው በውስጣችን ሊያሳድረው ስለሚፈልገው የመንግሥቱ ባህል ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የገዢው ባህል

*ባህልህ መገኛህን ያሳያል*

### የገዢው ንጉሣዊ ችሎታዎች

የመንግሥተ ሰማይ ባህል ከንጉሡ ባህርይ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ሁልጊዜም ልናስታው ስው የሚገባ ነገር ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጠባይና ስለባህሉ በሚንነጋገርበት ጊዜ፤ ስለ ራሱ ስለ ንጉሡ ችሎታዎች እየተናገርን ነው ማለት ነው። የገዢው ሚና ንጉሡን መወከል እስከሆነ ድረስ፤ የገዢውን ጠባይና አሠራሩን ለማየት እንችላለን፤ ንጉሡም ምን እንደሚመስል ድምዳሜ ልንሰጥ ይቻለናል። እንደዚሁ ደግሞ፣ መንፈስ ቅዱስ የሰማያዊውን ንጉሥ ባህርይ የሚያንጸባርቅ እስከሆነ ድረስ፤ የእርሱ ጠባይ የንጉሡን የተለየ ባህርይ የሚያሳይ ነው።

ይህ ጽንሰ ሀሣብ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ የተለመደ ነው። በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ገብተን ምግብ ስመብላት ብንቀመጥና አስተናጋጁ ጋጠወጥና ቸልተኛ ቢሆን፤ ስለ ምግብ ቤቱ ባለን አጠቃላይ ግምት ላይ አሉታዊ ጥላ ያጠላበታል። ነገር ግን፣ ወደ አንድ ጫማ መሸጫ መደብር ሄደን ደግሞ በዚያ የምንፈልገውን ነገር እንድናገኝ የሚረዳንን ጥበበኛና ትዕግስተኛ የሆነ ሰው ብናገኝ፤ እርሱ ስለሚሠራለት ድርጅት መልካም የሆነ አመለካከት ይኖረናል። አንድን ግለሰብ፣ የንግድ ደርጅት ወይም ተቋም በመወከል አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ሁኔታ፤ ስለተወከለው ሰው፣ የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም ባለን ግንዛቤ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

### የንጉሡ ባህርይ የመንግሥቱን ሁኔታ ይወስናል

የአንድ አገር ባህል የአገሩ ብሔራዊ ጠባይ እንደሆነ ተደርጐ ሊጠቀለል ይችላል። የአገሩ ባሕል የእምነቱ፣ የዝንባሌው፣ ለነገሮች የሚሰጠው ዋጋ (እሴት)፣ የመርሆዎቹ፣ የሕይወት ልምምዶቹና የጠባዮቹ ድምር ውጤት ነው። በአንድ መንግሥት ውስጥ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ዐይነትና ባህርያት እጅግ ወሳኝ ነገሮች ነበሩ፤ ምክንያቱም በሚገዛው ግዛት ላይ ተጽእኖ አሳድረዋል፤ አብዛኛውን ጊዜም ሁኔታዎችን



ይወስናሉ። በመንግሥቱ ውስጥ ሕይወት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ። ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

"በድሃ ህዝብ ላይ የሚገዛ ክፉ መኮንን እንደተራበ አንበሳና እንደተራበ ድብ ነው።"

"ጻድቃን በበዙ ጊዜ ህዝብ ደስ ይለዋል፣ ኀጥአን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ህዝብ ያለቅሳል።"

በሌላ አገላለጽ፤ የመሪው የባህርይ አቅጣጫ በመላው የሀገሪቱ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእስራኤል መንግሥት ታሪክ ሲፈጸምና በመጨረሻም መንግሥቱን ይሁዳና እስራኤል ወደሚባሉ ሁለት መንግሥታት እንደከፈለው እናያለን። የተለያዩ ነገሥታት ባህርይ በህዝቡ ላይ መልካም ወይም ክፉ ተጽእኖ ያሳድራል። ለምሳሌ ያህል፤ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ እንዲህ ተጽፎ እናነባለን፤ "የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ በእስራኤል ላይ ሁለት ዓመት ነገሠ። በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ በአባቱም መንገድ እስራኤልንም ባሳተበት መንገድ ሄደ። " ለለዚህ ሰው የተጻፈው ታሪክ እንደሚናገረው ድርጊቱ፤ "የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን አስቆጣ" ይላል። ኢዮርብዓም የእስራኤልን ህዝብ ጌታን መከተሉን ትቶ ጣዖታትን እንዲያመልክ አደረገው፤ በተጨማሪም ከሌዊ ልጆች ብቻ ካህናት ይሁኑ የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ፤ ካህን መሆን የሚፈልገውን ሰው ሁሉ ካህን እንዲሆን አደረገ። የእርሱ ልጅ የሆነውም ናዳብ በግልጽ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ ሄደ።

በተጨማሪም በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ስለ ሌላ ንጉሥ እንዲህ እናነባለን፤

"… አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። በናባጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ታናሽ ነገር መሰለው፤ የሲዶናውያንም ንጉሥ የኤትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤ ሄዶም በአልን አመለከ፣ ሰገደለትም። በሰማርያም በሠራው በበአል ቤት ውስጥ ለበአል መሠዊያ አቆመ። አክዓብም የማምለኪያ አጻድ ተከለ። አክዓብም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣውን ነገር አበዛ።"

እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጣው የኢዮርብአም ተግባር ጥቂት ነገር እንደሆነ ስለቆጠረ፤ አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ይልቅ የከፋውን ኃጢአት አደረገ። ክፉ የሆነው አመራር በእስራኤል ነገሥታት ሀረግ በተከታታይ ይቀጥል ነበር፤ ህዝቡም በክፉ ስራቸው ይገፋበታል። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ እንደሚዘግበው፤ በውጤቱ ህዝቡ ያተረፋት መከራን ብቻ ነበር። "የታሰረውና የተሰቀቀውም እንደጠፋ፤ እስራኤልንም

የሚረዳ እንዳልነበረ፤ እግዚአብሔርም እጅግ የመረረውን የእስራኤልን ጭንቀት አየ።”

በይሁዳ ግን፤ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ እንደተዘገበው ንጉሥ ሕዝቅያስን በምሣሌነት እናያለን፤

“እርሱም አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን አደረገ . . . ሕዝቅያስ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ታመነ። ከእርሱም በኋላ ከእርሱም በፊት ከነበሩት ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል አልነበረም። ከእግዚአብሔርም ጋር ተጣበቀ፤ እርሱንም ከመከተል አልራቀም፤ እግዚአብሔርም ለሙሴ ያዘዘውን ትእዛዛቱን ጠበቀ። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበር፤ የሚሄድበትም መንገድ ተከናወነለት።”

መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ የይሁዳን ህዝብ በበቀል ከተሞሉ ጨካኝ ጠላቶቻቸው እጅ እንደታደጋቸውና በነበሩበት አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ እንዴት መሆን እንደሚገባቸው ንጉሡ ሕዝቅያስ በተናገረ ጊዜ እንዴት እንደሰሙት ይዘግባል። ህዝቅያስን ባያምኑትና ለእግዚአብሔር የነበረውን ታማኝነት በምሳሌነት ባይቀበሉት ኖሮ በጠላቶቻቸው ወጥመድ ውስጥ ይወድቁ ነበር።

ለስኬታማ መንግሥት ቁልፉ የንጉሡ መልካም ባህርይ ነው። እንደዚሁ ሁሉ፤ የሰማያዊው ገዢ ባህርይ በምድር ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁኔታዎች ይወስናል። በተጨማሪም፤ የእርሱ ባህርይ በትክክል ከንጉሡ ባህርይ ጋር ተመሳሳይ ነው። በቅኝ ግዛት ውስጥ እርሱ የንጉሡን ባህርይ አኳኋን ይወክላል።

ንጉሡ የመንግሥቱን ባህርይ እንድንገነዘብ ይፈልጋል፤ በመሆኑም ልንተማመንበትና በእርሱም ውስጥ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን። ስለዚህ ነበር ኢየሱስ እርሱ ምን እንደሚመስል ለተከታዮቹ ያለማቋረጥ መግለጫዎችን የሚሰጣቸው፤

“እኔ መልካም እረኛ ነኝ፤ መልካም እረኛ ስለበጎቹ ነፍሱን ያኖራል።”

“እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አይራብም፤ በእኔ የሚያምን ሁሉ ዳግመኛ አይጠማም።”

“እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ ከልቤም ትሁት ነኝ፤ ለነፍሣችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።”



ኢየሱስ ስለባህርይው ሊያብራራላቸው ይፈልግ ነበር፤ ምክንያቱም በእርሱ ዘመን የኖሩ ሌሎች ነገሥታት የሚተገብሩት ተቃራኒ የሆነውን ባህርይ ነበር። ለምሳሌ ያህል፤ አንድ ጊዜ ደቀመዛሙርት ከእነርሱ መካከል ማን ታላቅ እንደሆነና የበለጠውን ክብር እንደሚቀበል እርስ በእርሳቸው ይጨቃጨቁ ነበር። ኢየሱስ ይህንን ክርክር የሰማያዊውን መንግሥት ባህርይ ለማብራራት እንደ ምክንያት ተጠቀመበት። በማቴዎስ መጽሐፍ የተዘገበው ቃሉ ይህን ይመስላል፤

“የአህዛብ አለቆች እንዲገዟቸው፤ ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም። ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።”

ለስኬታማ መንግስት ቁልፉ የንጉሡ መልካም ባህርይ ነው

በዚህና በሌሎች ብዙ መንገዶች፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እነርሱ ይኖሩበት ከነበረው ከጨለማው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የተለየ እንደሆነ ያለማቋረጥ ለማስተማር ሞክሯል። ያለማቋረጥም የንጉሡን ጠባይና ባህርይ በመግለጽ መልካም ስለሆነው መሪ እውቀት እንዲኖራቸው ይፈልግ ነበር።

ጠቅላላ የንጉሡን ባህርይ የማወቅ ሀሳብ አሳሳቢ ነገር መሆኑን፤ “የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች” ከሚለው የኢየሱስ ቃል እንረዳለን። የዚህ የተለየ መንግሥት ዜጎች እንድንሆን ይጋብዘናል፤ ስለ መንግሥቱም ባህርይ ምንነት ሊያረጋግጥልን ይፈልጋል።

## የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ የመንግሥትን ባህል ማሳደግ ነው

ጳውሎስ የሰማያዊውን መንግሥት ባሕርይ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ዜጎች ሕይወት ለማሳደር ፈልጎ ነበር፣ እነርሱም ከንጉሡ ጋር መስለፍ (መስማማት) ማለት ለነርሱ ምን ማለት እንደሆነ ይማሩ የነበሩ ነበሩ። በገላትያ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች በጻፈው ደብዳቤ የንጉሡን ባህርይ የሚያሳዩ አስፈላጊ ጠባያትን ዝርዝር አቅርቧል፤

- ፍቅር
- ደስታ
- ሰላም
- ትዕግስት
- ቸርነት
- በጎነት
- እምነት
- የውሃት
- ራስን መግዛት

በምድር ላይ የትኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ እነዚህ ባህርያት ይኖሩታል። ጳውሎስ እነዚህን ጠባያት፤ "የመንፈስ ፍሬ" ሲል ይጠራቸዋል። ገዢው ባለበት ስፍራ ሁሉ እነዚህ ባህርያት እየተገለጡ የመንግሥቱ ባህል በዚያ እንዳለ ማስረጃዎች ሲሆኑ ይገባቸዋል።

ጳውሎስ እነዚህን ጠባያት በፍሬ የመሰለበት ምክንያት ፍሬ በአንድ ሌሊት ስለማይታይ ነው፤ ከጊዜ ጋር እያደገ ይሄዳል። እናም በገዢው ምሣሌነትና አመራር የንጉሡን ባህል በሕይወታቸው እየተንከባከቡ ማሳደግ እንደሚገባቸው ያውቁ ዘንድ ይፈልግ ነበር። በመጀመሪያ፤ ገዢው በሰማይ የሚገኘውን እውነተኛ ባህርይ ያስተምረናል። በመቀጠልም እርሱ በእኛ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ምክንያት ይህ የመነሻ ባህርይ በእኛ ዘንድ እንዳለና በሕይወታችን ልንገልጸው እንደሚገባን ያሳየናል።

መንፈስ ቅዱስን በምትቀበሉበት ጊዜ፤ የመንግሥቱን ባሕርይ ዘር ደግሞ ትቀበላላችሁ። በሕይወታችሁ ውስጥ ዘሩ እንዲያድግ የሚያደርጉትን የመንግሥቱን ባሕርያት በመጨመር ይህንን ዘር ታሳድጉታላችሁ። ለምሳሌም፤ አንድ የፖም ዛፍ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ዛፉ "መስራት" አያስፈልገውም። የዛፉ ፍሬ ዘር በራሱ ውስጥ አለ፤ እናም ቀስ እያለ በእድገት ሂደት ውስጥ፤ አስፈላጊ የሆኑ ግብዐቶችን ማለትም በመሬት ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮችንና የጸሀይ ብርሃንን በመጠቀም በቅርንጫፎቹ አማካይነት ፍሬው መገለጥ ይጀምራል። ፍሬው በሕይወታችን ውስጥ እንዲያድግ የሚያስችሉት መንፈሳዊ ንጥረ ነገሮች፤



ከንጉሡ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነትን መቀጠል፤ የመንግሥቱን ህገ መንግሥት ማጥናት - ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ እንዲሁም በውስጣችን ለሚኖረው ገዢ ምሪት ራሳችንን መስጠት ናቸው።

ልክ የፖም ፍሬዎች ከፖም ዛፍ መገኘታቸው ተፈጥሯዊ እንደሆነ ሁሉ፤ የመንፈስ ፍሬ በአንድ የመንግሥቱ ዜጋ ሕይወት ውስጥ ማደጉ የተለመደ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ የሚያንጸባርቀው የንጉሡን ባህርይ ነው። ለምሳሌ ያህል ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ በጎነት ነው። በመሆኑም በመንግሥቱ ውስጥ የምንኖር ከሆነ በጎዎች መሆናችን የተለመደ ነገር ነው። በጎዎች ካልሆንን ግን ልንሆን የተገባንን ዐይነት ሰዎች አይደለንም። ገዢው ዋና (የመነሻ) ከሆነው ባህርያችን ጋር ያገናኘናል፤ ይህም እንደ ሰው ልጅነታችን ለእኛ የተገባ እውነተኛ ሕይወት ነው።

> የንጉሥ - ሰባት
>
> ባህል በፍቅር፣
>
> በደስታና በሰላም
>
> ይታወቃል

የመንፈሱ ጠባይ ወይም ፍሬ የሚያሳየው የንጉሡን ባህል ነው፤ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ የፍቅር ባህል፣ የደስታ ባህል እንዲሁም የሰላም ባህል መሆኑን እናያለን። ከላይ በተጠቀሰው ዝርዝር በተመለከቱት ጠባያት የተሞላ ባህል ምን እንደሚመስል ገምቱ! ለተሰጡን ሃላፊነቶች ታማኝ መሆን የእኛ ባህል ነው። የዋሃት ባህላችን ነው። ከሌሎች ሰዎች ጋር ግብስብስ ወይም ባለጌ ልንሆን አይገባም። ኢየሱስ "ትሁታን ብጹዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉ" እንዳለው ራስን መግዛት የእኛ ባህል ነው። ፍላጎቶቻችንን ወይም ቁጣችንን በጭራሽ ከቁጥጥር ውጭ ሲሆኑ አይገባም። በሕይወታችን ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢፈጠር እነዚህን ጠባያት ይዘን በመጽናት መኖርና ማሳየት አለብን።

በእኛ ውስጥ የሚኖረው ንጉሣዊው ገዢ በሚኖርበት ጊዜ፤ የንጉሡን ባህርይ እንድናጸባርቅ በማስቻል ሕይወታችንን ያድሰዋል። ለሕይወት አዲስ እይታና የመንግሥቱን አዲስ ሥርዓተ ትምህርት በመስጠት ግላዊ የሆነውን ባህላችንን ይቀይረዋል። የንጉሡ የአመለካከት ቅኝት እንዲኖረንም ያደርጋል። እንዴት እንደምናስብ፣ እንዴት እንደምንናገር እንዴትስ እንደምንመላለስ እንደገና ያስተምረናል።

### ባህል መገኛውን ይገልጻል

ባህልህ መገኛህን መግለፁ የግድ ነው። ምግባርህ፣ ለሌሎች የምትሰጠው ምላሽ፣ ችግሮችን የምትጋፈጥበት መንገድና ግራ መጋባቶች በተከሰቱ ጊዜ የምትሰጠው ምላሽ ሁሉ የሰማያዊውን መንግሥት ባህል የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። በአንተ ውስጥ ያለው የመንፈሱ ጠባይ

ነው፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩ እነዚህን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም"

በዚህ ስፍራ " መውረስ" የሚለው ቃል በመንግሥቱ ውስጥ መኖርን ወይም መመሳሰስን ነው፡፡ የመንግሥተ ሰማይ ባህልና ዓለማዊ የሆነው ባህል ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ ባዕድ በሆነ ባህል ውስጥ እየኖርክ በመንግሥተ ሰማይ መመሳሰስ አትችልም፡፡

የገዢው ሚና የመንግሥቱን ዜጎች ንጉሡ በተመሳሰበት የሕይወት ዐይነት ስመስወጥ እስከሆነ ድረስ እኛ በጨለማው ባህል ዐይነት መመሳሰስ በምንጀምርበት ጊዜ ይገስፀናል፣ ያርመናል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው በሁለት መንገዶች ነው፤ በመጀመሪያ አዕምሯችን ማስጠንቀቂያ በሚያሰማበት ውስጣዊ ሥርዓት ይጠቀማል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የንጉሡን ትምህርት እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡ በመንግሥቱ ህገ መንግሥት ውስጥ የተዘገበውን ወደ አዕምሯችን ያመጣል ወይም የንጉሡን የተጻፈ ቃልና መንገዶች - ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው - እንድናስብ ያደርገናል፡፡ ጳውሎስ፣ "ከህግ በታች" የማንኖር ሰዎች መሆናችንን ጽፎልናል፡፡ በሌላ አገላለጽ፤ "አድርግ" እና "አታድርግ" የሚሉትን ህጎች አጥብቀን ስመከተል የምናደርገው ሙከራ አይሠራም ማለት ነው፡፡ የተለወጠ ባህርይ ብቻ ነው ንጉሡ የኖረውን አይነት ሕይወት እንድንኖር የሚያስችለን፡፡ ገዢውም ይህንን አዲስ ባህርይ ይሰጠናል፣ እንድንከተለውም ያስችለናል፡፡

> ንጉሡ የኖረውን ዐይነት ሕይወት እንድንኖር የሚያስችለን የተለወጠ ባህርይ ብቻ ነው

"ንግግር ከዙፋን" የተባለውን በንጉሣዊ ገዢው በኩል የእንግሊዝ ንግሥት በባሃማስ ለሚኖሩ ዜጎች ያላቸው ፈቃድ ነው ተብሎ የሚነበበውን እናስታውስ፡፡ ከሰማያዊው ዙፋን የሆነውን ንግግር ቅዱሳት መጻሕፍት አስፍረው .የዘዋል፡፡ ከመጻሕፍቱ ጋር በቅርብ ስንተዋወቅ፤ ገዢው የንጉሡ ፈቃድ ምን እንደሆነ ያስተምረናል፤ ያሳስበናልም፡፡ "አንተ ይህንን ለማድረግ አቅደሃል፤ ይሁን እንጂ ንጉሡ ለአንተ መልካም ነው ያለው ይህ አይደለም፡፡ ይህ እኮ ከሰማያዊው ዙፋን በሆነው ንግግር ውስጥ የተጻፈ ነገር አይደለም" እያለ ይነግረናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ከዙፋኑ በሆነው ንግግር መሠረት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ያ የንጉሡ ሀሳብ ነው፡፡ እንደገናም፤ የእኛ ተግባር የሚሆነው፤ "የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ የአንተ ፈቃድ ግን ይፈጸም" ብሎ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፡፡ እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው፡፡ ሕይወትም ነው፡፡"



በአዲሱ ዋና መምህር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥር እንደሆንህ ማስታወስ ይገባሃል፡፡ በአዲስ የሕይወት ፍልስፍና ሥር ነህ፡፡ የአዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተማሪም ነህ፡፡ የአዲስ አመለካከት ዘይቤ ባለ አደራ ነህ፡፡ ሌሎችን ትምህርት ቤቶች ሁሉ ጥለህ፤ ለመንግሥቱ ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ ራስህን ሰጥተሃል፡፡ እናም ገዢው የንጉሡን ትምህርት ከሕይወትህ ጋር ሊያዋህድና እንድትገልጸውም ሊያስችልህ የአንተ የግል መምህር ነው፡፡ እርሱ በንጉሥ ልጆች ውስጥ የመንግሥቱን ባህርይ ለማሳደር እንደሚታጋ ንጉሣዊ አስጠኚ ነው፡፡ የመንግሥተ ሰማይ ወራሽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ልንለማመድ ያስፈልገናል፡፡

ገዢው፤ ልክ ንጉሡ - ልጅ እንዳደረገው ፈጣሪን እንደገና እንደ አባታችን እንድንቆጥረውና "አባ አባት" ብለን እንድንጠራው በማስቻል ማስተማሩን ይጀምራል፡፡ ይህ ዝምድና እንደገና በፈጣሪያችን መልክ እንደገና እንድንሠራ ያስችለናል፡፡ የእርሱን ባህርይ ማንጸባረቅ የማያስችለንን ብቃት ያጣነው በዐመጽ ምክንያት ነው፡፡ ከጨለማው መንግሥት ጋር ቀድሞ በነበረን ግንኙነት ሳቢያ ያ ባህርይ በውስጣችን ተዘባርቋል፡፡ ገዢው፤ እኛ አስቀድሞ የተፈጠርነው ለምን እንደሆነ የማስተማር ከባድ ሥራ አለበት፡፡

> የመንፈስ ፍሬ ንጉሡ የተገበራቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ እነርሱ እርሱ ራሱ ናቸው፡፡

እየተመለከትናቸው ያሉ ችሎታዎች ወይም የመንፈስ ፍሬ በንጉሡ የተተገበሩ ብቻ ሣይሆኑ እነርሱ እርሱ ራሱ ናቸው፡፡ ንጉሡ ነገሮችን የፈፀመው በፍቅር ብቻ አልነበረም እርሱ ራሱ ፍቅር ነው፡፡ ያሳየው ሰላም ማለት ምን እንደሆነ ብቻ አልነበረም፤ እርሱ ራሱ ሰላም ነው፡፡ የትኛውም የንጉሡ ባህርይ ይሁን፤ በእኛም ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ሊገለጥ የተገባው ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ እንደተዘገበው "የሰማዩ አባታችን ፍጹም እንደሆነ፤ እናንተ ደግሞ ፍጹማን ሁኑ" ሲል ይህን ማለቱ ነበር፡፡

የንጉሥ አባታችንን ባህርይ ማንጸባረቅ እንደሚገባን ማወቃችን፤ ወደ የግል መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና ስጋችን ባህል ምን መግባት እንዳለበት ጠንቅቀን እንድንጠብቅ ያደርገናል፡፡ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት፣ በእናንተ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በስጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡" ጳውሎስ እየተናገረ ያለው፤ "ሰውነታችሁ የገዢው መኖሪያ ቤት እንደሆነ አታውቁምን? እርሱ ቅዱስ ነው፤ በእናንተም ውስጥ ይኖራል፡ በመሆኑም ማደሪያውን በንጽህና ልትጠብቁለትና እንደባህርይውም ልታዘጋጁለት

በዚያው መጠን ጐን ለጐን መሠረታዊ የሆኑ የመንግሥቱን ባህርያት በውስጣቸው የማላደግ ወላኝነቱን አይገነዘቡትም። የመንፈስን ፍሬ በሕይወታችን ከማፍራት ይልቅ፤ የመንፈስን ስጦታ መቀበል ይቀላል። የእግዚአብሔርን ባህርይ በሕይወታችን ከማሳደግ ይልቅ፤ የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት ይቀላል። በመሆኑም፤ እንደ ፍቅር፣ በጎነትና ራስን መግዛት የመሳሰሉትን ባህርያት ማሳደግ የግድ ነው፤ ምክንያቱም የስጦታ አጠቃቀማችን የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጉታል።

ባህርያቱም ሆኑ ስጦታዎቹ ሁለቱም ጠቃሚዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ ባህርያቱ ወሳኝ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፤ ምክንያቱም ኃይል ያለ ባህርይ አጅግ አደገኛ ነው። እነዚህን ሁለት ነገሮች ማመጣጠን በሁሉም የመንግሥቱ ዜጎች ዘንድ ትልቅ ተግዳሮት ነው። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ እንዴት እንደሚኖሩ፣ እንዴት እንደሚያስቡና እንዴት እንደመንግሥቱ ዜጎች እንደሚተገብሩ በማስተማር ሦስት ዓመት ተኩል የፈጀው ለዚህ እንደሆነ እምናለሁ። በመጀመሪያ አሰለጠናቸው፤ ቀጥሎም በበዓለ ሃምሣ ቀን በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የሰማያዊውን መንግሥት ኃይል ተቀበሉ። በተጨማሪም፤ ወደ መንግሥቱ ባህል የመሰወጥ ተግባር ቀጣይና የሕይወት ዘመን ሂደት በመሆኑ፤ እርሱ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላም ገዢው እነርሱን ማሠልጠኑን እንደሚቀጥል ነግሯቸዋል።

## የባህል ተጽእና

በመጨረሻውም፤ ባህል ተጽእኖ በማምጣት እንደሚስፋፋ ሁሉ፤ የመንፈስ ቅዱስ ባህርያትና ስጦታዎች በምድር ላይ የሰማያዊው መንግሥት ተጽእኖ ማላደሪያዎች ናቸው። ገዢው ሕይወታችንን ወደ ንጉሡ ባህርይ እንዲለውጥ እስከፈቀድንለትና ኃይሉንም መግለጥ ስንጀምር ሕይወታችን በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽእኖ ያመጣል። ሰማያዊው መንግሥት በምድር ላይ የሚስፋፋው በዚህ መንገድ ነው። ጴጥሮስ፤ በበዓለ ሃምሣ ቀን የወረደው መንፈስ የንጉሡ የተስፋ ቃል ፍጻሜ መሆኑን በገለጸ ጊዜ፤ በዚያ ስፍራ ተሰብስበው በነበሩ ሰዎች ላይ ያመጣው ተጽእኖ ኃይለኛ ነበር፤

> "ቃሉንም (ስለመንግሥቱ) የተቀበሉ (የጴጥሮስን)፤ ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በህብረት እንጀራንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በለው ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ተእምራት ተደረገ። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉ ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር። እግዚአብሔርንም



> እያመሰገኑ በህዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።"

ይህ አስደናቂ የሆነ የባህል ለውጥን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው! አማኞቹ ያሳዩት ፍቅር፣ ያላቸውን በጋራ መካፈላቸው፣ ትምህርታቸውና የመንግሥቱን ኃይል የመግለጥ ተግባር እነዚህ ሁሉ የመንግሥቱ ባህል ማንፀባረቂያ ናቸው፤ ይህን አዲስ መንግሥታዊ የሕይወት ዘይቤ በዓይኖቻቸው በተመለከቱ ሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስን አቀዳጃቸው፣ በመሆኑም የሰማያዊው መንግሥት ተጽእኖ በምድር ላይ በየዕለቱ እያደገ ይሄድ ነበር።

በንጉሣዊ ገዢ ሥር እንዳሉ ምክትል ገዢዎች የመንግሥቱ ባህል አምባሳደሮች ሆነን እናገለግላለን። መንግሥታዊው ተጽእኖ ከአንድ ግላዊ መሰጠት ጀምሮ ወደ ማኅበረሰብ፣ አገር አቀፍ ከዚያም ዓለም ዓቀፋዊ ወደሆነ ለውጥ ያድጋል። ይሁን እንጂ የሚጀምረው ራሱን ከጨለማው መንግሥት ባህል ወደ የሕይወትና ብርሃን መንግሥት ከለወጠ አንድ ግለሰብ ነው። አንተ እሁን የተሰለፍከው ከየትኛው መንግሥት ጋር ነው?